ኦቴኖ፡- የአኙዋ ባህላዊ ጀግና

ባይለየኝ ጣሰው

1. መግቢያ

እንደ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ናይሎ ሰሃራ ወገኖች ሁሉ የአኙዋ ህብረተሰብንም ቃላዊ ህብረተሰብ (oral society) ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም የዕምነት ስርዓቱ፥ ስነምግባራዊና ማህበራዊ እሴቶቹ፥ ደንቦቹና ሕጎቹ፣ አመለካከቱ፥ አስተሳሰቡ፥ የኑሮ ፍልስፍናው፥ የረዥም ዘመናት የዕውቀት ክምችቱ፥ የፈጠራ ክሂሉና ጥበቡ ሁሉ ተከማችቶ የሚገኘውና የሚገለጸው በስነቃሉ አማካይነት በመሆኑ ነው። Peacock 1969:167 "ቃላዊ ህብረተሰብ እንደ ስነቃል ነው። ምክንያቱም በአንድ ትረካ ውስጥ የሚገኘው መዋቅር የህብረተሰቡን መዋቅር ስለሚመስል ነው" ይላሉ። ስለዚህ እንደ አኙዋ ያለውን ቃላዊ ህብረተሰብ ለማወቅ ስነቃሉን መመርመር አስፈላጊ ይሆናል ማለት ነው። ምንም እንኳን የስነቃል ጥናት ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑ ቢታወቅም በአገራችን ለዕድገት በሚበጅበት መልኩ ተሰብስቦና ተጠንቶ አይገኝም። (Kunene ም 1980: 205) የአፍሪካ ዘመናዊ የስነጽሑፍ ምሁራን የአፍሪካን ኮስሞልጂያዊ (የስነፍጥረትና ስነህላዌ) እምነቶችን፥ ጥልቀት ያላቸው ሃተታ መናፍስትን፥ ገድሎችንና ትረካዎችን ቢመራመሩና ቢተረጉሙ ድንቅ የሆኑና የላቁ ስራዎችን በማፍለቅ "ለአፍሪካ ዘመናዊ ስነጽሁፍ ዳግም ልደት" ሊያበስሩ መቻላቸውን ያስገነዝባሉ። ስነቃል የሚጠናው ጥንት ምን ይደረግ እንደነበረ ለማስታወስ ብቻ አይደለም፣ ይልቁንም ስነቃል የሰው ልጅ የተከማቸ ዕውቀት የሚገኝበት ሰፊ መስክ በመሆኑ ለዛሬው ዘመን ዕድገት መሰረት ለመጣል ይጠቅማል (Campbell 1960: 36)። በአገራችን የስነቃል ጥናት ሊኖረው የሚችለውን ፋይዳ ፈቃደ (1970፥ 9)፥ "የዛሬው ትውልድ የቆመበትን መሰረት፣ ዛሬ የራሱ ብቻ ሳይሆን የትናንቱም ውጤት ነውና ትናንትን ማወቅ ዛሬን ለማወቅና የነገውንም መንገድ ለማቀድ ስለሚበጅ አፋዊ ኪነተ ቃል አንድን ሕዝብ የማወቂያና የዛንም ሕዝብ መለወጫ መንገድ መፈለጊያ መሳሪያ ሊሆን ይችላል" ሲሉ ገልጸውታል፡፡ የዚህ ጥናትም ትኩረት በአኙዋ ህብረተሰብ ውስጥ በባለ ታሪኩ ስም "ኦቴኖ" ተብሎ የሚታወቀው ትረካ በሚሰጠው ስነጽሁፋዊ ትርጓሜ ላይ ይሆናል። ለመመለስ የሚሞከራቸው ዋና ዋና ጥያቄዎችም፥ ኦቴኖ ምን ዓይነት ጀግና ነው? በባለታሪኩ ገድል፥ ዕጣና ዕድል እንዲሁም በተሰጡት ሰብአዊ ባህርያት አማካይነት አኙዋዎች ስለተፈጥሯዊው ዓለም ሥርዓትና ስለራሳቸው ያላቸውን ግንዛቤና እምነት እንዴት ይገልጹታል? የሚሉ ናቸው። ኦቴኖ በባህሉ ላይ ያምጻል። ባህሉም ኦቴኖን አይቀበለውም። በጥርጣሬና በስጋት ያየዋል። ስለዚህ ኦቴኖ የሚኖርበት ዓለም ለምን በስጋት እንደሚያየው ይጠይቃል። በታሪኩ ውስጥ እንደምናየው የግጭቱ መነሻ የእምነት ጉዳይ ይሆናል። ስለዚህ ኦቴኖ የእምነት መሰረቱን ያናጋዋል። ሆኖም በህብረተሰቡ ህይወት ላይ አንድ አሻራ ጥሎ ያልፋል፡፡

2. ባህላዊ ጀግና ምንድን ነው?

"ባህላዊ ወይም ትውፊታዊ ጀግና ምንድን ነው?" ለሚለው ጥያቄ የተጠቃለለ መልስና ቁርጥ ያለ ብያኔ ተሰጥቶት ይገኛል ለማለት አያስደፍርም። ፓስካል (1990: 2-4) እንደሚገልጸው ይህ ዓይነቱ ችግር የሚመነጨው "ባህል"፥ በተለይም "ትውፊት" (tradition) ለሚለው እሳቤ በተለያዩ የስነሰብዕ (humanities) የጥናት መስኮች የተለያዩ ምሁራን እንደየትምህርት ቤቶቻቸው የአስተሳሰብ ቅኝት ከሚሰጧቸው ትርጓሜዎች የመነጨ ይሆናል። አንዳንዶቹ ትውፊትን እንደ አለፈ ታሪክ፥ እንደ አጽመ-አካል ይመለከቱታል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ከህብረተሰብ የአስተሳሰብ አድማስ ጋር የሚያድግና በሁባሬነት የሚገኝ ነው በማለት ተለዋዋጭነቱንና ሂደታዊነቱን ይቀበላሉ (Muana 1998,42-45)። ስለትውፊታዊ ጀግኖች የሚቀርቡ ብያኔዎችም ከእነዚህ አመለካከቶች ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው በሁሉም ዘንድ ሁለንተናዊ ተቀባይነት ባለው መልክ ሠፍረው ይገኛሉ ማለት አይቻልም።

ይሁን እንጂ Birds እና ኬንዳል (1980)፥ እንዲሁም Frye ፍራይ´ (1957) ስለሚት፥ ካምፐቤል (1960) እና Raglan (1965) ስለ ባህል ጀግኖች በየበኩላቸው ያሠፈሯቸው ተግባራዊ ብያኔዎች፥ ሃሳቦችና ያስቀመጧቸው መርሆዎች ይህ ጥናት መመለስ ለሚሞክራቸው ጥያቄዎች አቅጣጫ ሰጭ (paradigm) ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ Birds እና ኬንደል (1980: 13) ጀግና የሚኖርበትን ሕብረተሰብ ልማዳዊ ሕጎችና ˙ ወግ አጥባቂ ኃይሎችን ለመቃወም የሚጠቅም ልዩ ኃይል የተሰጠው ሚዛን የሚያፋልስ (agent of disequilibrium) ሆኖ እንደሚታይ ይገልጻሉ። ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት፥ አንደኛ የባህል ጀግናው ድርጊት ተለምደዊውን ምግባር ይፃረራል፤ ሁለተኛ ጀግናው ገድል ከሚሠራበት ህብረተሰብ አውድ ውጭ አይሆንም፤ ሦስተኛ ተግባሩ ከሌሎች ሰዎች ድርጊት በተፃራሪ እንደመቆሙ ሁሉ በማህበረሰብና በግለሰቦች በልማዳዊና በአፈንጋጭ መርሆዎች መካከል የሚኖርን ግጭት የሚያመለክት ይሆናል የሚሉ ናቸው። Frye (1957: 33-35) በበኩሉ የአሪስቶትልን ፖየቲክስ (poetics) መሠረት በማድረግ የገጸባህርያት ድርጊቶች ከዕውኑ ዓለም ሰዎች ድርጊቶች ልቀው እንደሚቀርቡና ልቀቱም ሶስት ደረጃዎች እንዳሉት ይተነትናሉ። በትንተናው መሰረት አንድ ጀግና (hero) ከሌሎች ሰዎችና ሰዎቹ ከሚኖሩበት አካባቢ ልቆ ከቀረበ መለኮታዊ ፍጡር እንደሚሆን፥ የታሪኩ ቅርጽም "ሚት" እንደ ሆነና ልቀቱም የዓይነት እንጅ የደረጃ ሊሆን እንደማይችል ያስረዳሉ።

ነገር ግን ባለታሪኩ በአቀራረቡ ከሌሎች ሰዎችና እንዲሁም ከራሱ አካባቢ ልቆ ሲቀርብ ልቀቱ "የዓይነት" ሳይሆን "የደረጃ" እንደሚሆን፥ እሱም እንደ "መለኮታዊ"ም እንደ "ሰው ፍጡር"ም እንደሚታይና የታሪኩ ቅርጽም "ሮማንስ" እንደሚባል ፍራይ ይገልጻሉ። ሮማንስንም እንደ ገና በሁለት ይከፍሉታል። "ዓለማዊና መንፈሳዊ" በሚል። ኦክፔሁም (1980:13) እንደዚሁ ፍራይ ዓለማዊና መንፈሳዊ በሚል የከፈሏቸውን "ታሪካዊና ሮማንቲክ-ሚቲክ-ሌጀንድ" ይሏቸዋል። በተለይም ፍራይ እንደሚገልጹት፥ በዓለማዊም ሆነ በመንፈሳዊ መልኮች የሚቀረጹ የሮማንስ አይነተኛ ጀግኖች (typical heroes) እኛ ሰዎች በተፈጥሮአችን

ልናከናውነው ከምንችለው በላይ በላቀ ጀግንነት፥ አይገቴነትና ጽኑነት የሚወጡና ከተለመዱት የተፈጥሮ ሕጎች ውጭ በተአምር ገድል ወይም ጀብድ የመፈጸም ኃይል ተሰጥቷቸው የሚቀርቡ ናቸው።

ሦስተኛው የባህል ጀግና እንደ ሚት ወይም ደግሞ እንደ ሮማንስ ጀግና ከአካባቢው የላቀ ሳይሆን እንደ እኛ፥ እንደ ሰዎች፥ ለተፈጥሮ ሕጎች ተገዥ ሆኖ የጀግናው ልቀት ከሌሎች ሰዎች ደረጃ አንጻር ብቻ የሚነጻጸር፥ የሩቅ ዓላማ ያነገበ፥ ህይወቱ በፈተና የተሞላና በአሪስቶትል አእምሮ ይጉላላ የነበረው ዓይነት የትራጀዲ ጀግና ነው። ፍራይ እንደሚያስረዱት፥ ከእነዚህ ውጭ በማንኛውም ገጽታ ከሰው እኩል ደረጃ ይዘው የሚቀርቡ የዘመኑ ገጸባህሪያት አሉ። ነገር ግን በተጠቀሱት፥ ማለትም በሚት፥ በሮማንስና በትራጀዲ ጀግኖች መካከል ልዩነቶችን ቁርጥ ባለ ሁኔታ የማስቀመጡ ሙከራ አስቸጋሪነት እንዳለው Frye እንዲህ ሲሉ ገልጸውት እናገኛለን፤

> *Where a religion is mythological and polytheistic, where there are promiscuous incarnations, deified heroes and kings of divine descent, where the same adjective "godlike" can be applied either to Zeus or to Achilles, it is hardly possible to separate the mythical, romantic, and high mimetic strands completely (1957: 35).*

የባህል ጀግኖች አፈጣጠር ከአንዳች መለኮታዊ ኃይል ጋር ቁርኝት ጠው ሲሆን የሚጓዙበት የህይወት ጎዳና በጀብድ፥ በገድልና በተአምር የተሞላ ባላቸው ደረጃ መሠረትም ሁለንተናዊና አካባቢያዊ፥ ልዕለ–ተፈጥሮ rnatural)፥ ዲበ ኩሉ፥ ወይም ልዕለ–ሰብዕ (superhuman) ሊባሉ ይችላሉ። ደረጃቸው በአካባቢያቸው መንፈሳዊ ወይም ቁሳዊ ህይወት ላይ የየበኩላቸውን አሻራ ጥለው ወይም አንድን እሴት አበርክተው ያልፋሉ። ለምሳሌ ቴየስ እሳትን ከአማልክት ሰርቆ ለሰው ልጅ አበርክቷል። ሙሴ አሠርቱ ትዕዛዛትን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ ለተከታዮቹ ሰጥቷል። ጉታማ (ቡደሓ) ብቻውን ተገልሎ ለብዙ ጊዜ በጽሞናና በአርምሞ በጥልቀት በማሰብና ከፈጣሪው ጋር በመገናኘት የተገለጸለትን "መልካሙን ሕግ" ለህንዶች እንዳስተማረ ይተረካል። የቻይናው ፉሕሲ የከብት እርባታን፥ ዓሳ ማጥመድንና የአደን ጥበብን ለጥንታዊ ቻይናውያን አስተምሯል ተብሎ ይነገራል። ሽኑንግ እርሻንና የአዝርዕት አጠቃቀምን፥ ሁዋቲንግ ደግሞ ያለማቋረጥ ለሦስት ወራት ከእንቅልፉ ሳይነቃ በመተኛት በሕልም ተጉዞ ከመናፍስት ጋር በመገናኘት ተምሮ ወደ ሰባ የሚሆኑ የዕፀዋት መድኃኒቶችን፥ የአስተዳደር ሥርዓትን፥ የቀንና የወራት አቆጣጠርን፥ የሸክላና የብረታ ብረት መቅለጥንና ብየዳ ጥበብን ለመጀመሪያ ጊዜ ለጥንታዊ ቻይናውያን አስተምሯል ተብሎ ይተረካል።

የባህል ጀግኖች በጊዜም፥ በቦታም በዕውን ተለይተው ከሚታወቁት የታሪክ ጀግኖች (historical heroes) የተለዩ ናቸው። የተለዩ የሚሆኑበት ምክንያትም የባህል ጀግኖች የምናብ ዓለም ፍጡሮች በመሆናቸው ነው (Raglan 1965: 142-145)። Raglan የባህል ጀግኖችን አጥንተዋል። ከእነዚህ የባህል ጀግኖች መካከልም ለኦቴና ቅርብ ጎረቤት የሆነው የሹሉኩ ኝካንግ ይገኝበታል። ኝካንግ የተወለደው ከአዞ

ንግስት ነው ተብሎ ይታመናል። በተአምራዊ ኃይል ከመሰወሩ በፊት ኝካንግ ሹሉኮቹን እንደ ሕንዱ ጉታማ ሕግ አስተምሯል ተብሎ ይተረክለታል። ከሹሉኮች ሌላ የአኙዋ ደንበርተኛ በሆነው በኑወር ማህበረሰብም ሙንደንግ የፈጣሪ፥ የጁቅ፥ መልዕክተኛ (yäfät'ari mälɨktäña) ተብሎ የሚጠቀሰው ትንቢተኛ በየዘመኑ የሚከሰቱትን አዳዲስ ለውጦች አስቀድሞ መተንበዩ እንደዚሁ ይነገራል። በ ህብረተሰብ ውስጥም በተመሳሳይ ሁኔታ ሌር የተባለው አምላክ የንብ ዘደን፥ የአዝርዕት አጠቃቀምን፥ እንዲሁም የአደን ጥበብንና የሥራ (division of labour) እንዳስተማረና እነሆ መዠንግሮች ኑራቸው እስከ ዛሬ በዚያው ተወስኖ እንደ ቀጠለ ይናገራሉ (Stauder 1971:14)። ከላይ እንደተ ምሳሌዎች ሁሉ አኙዋዎችም ለመጀመሪያ ጊዜ ከውሃ ወጥቶ በመምጣት ሥርዓትን (kingship sytem) የፈጠረና ክወር የተባለውን መተዳደሪያ ሕግ ያ በኋላም ተመልሶ ወደ ውሃ የገባ፥ ውሃ ውስጥ የሚኖር ኦሹዶ የሚባል መለኮታዊ ፍጡር አለ ብለው ያምናሉ (Bayleyegn 2000: 5-32)። በአጠ ከዚህ በላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች የምንረዳው፥ የባህል ጀግኖች በተፈ ህብረተሰብ ህይወት ላይ አንድ ፋይዳ ያለው ነገር ጥለው የሚያልፉ መሆ ነው። መሰረታዊ ዓላማቸው ሃይማኖታዊም ይሁን ፖለቲካዊ፥ የባህል ጀግኖች ልጅ ምናባዊ የፈጠራ ኃይል ውጤቶች ናቸው። እንደ ውቅያኖስ በሰፉት እንደ ኦሬንታሉ ምናባዊ ዓለሞች ወይም እንደ ግሪክ ሚቶችና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ በተአምራትና በገድሎች ያሸበረቁ የባህል ጀግኖች የህይወት ታሪኮች፥ ወጣም ወረደ፥ የሚከተሉት አንድ ተመሳሳይ ፈለግ አለ። Campbell እንደሚገልጹት፥ ይሄው ተመሳሳይ ፈለግም ከመነሻ እስከ መድረሻ ዙሮ ገጠም ሁረት የሚከተል ይመስላል። ይህን ፈለግም Campbell በጥቅል *"a separation from the world, a penetration to some source of power and a life-enhancing return"* በማለት ይገልጹታል (1960: 30-38, 315)።

የባህል ጀግናው በዚህ ዕጣው በሚጓዝበት መዘውራዊ ሁረት ውስጥ ከአባቱ ወይም ከወንድሙ ጋር ከመፋለም አንስቶ በዓሳ ነባሪ እስከመዋጥ፥ ከደራጎን ጋር ከመተናነቅ በመስቀል እስከ መቸንከር፥ በጥቅጥቅ ጭለማ ውቅያኖስ ለማቋረጥ ከማቃተት አንስቶ አከላቱ ተቆራርጦ፥ ስጋውና አጥንቱ ተደቁሶ ለነፋስ እስከ መበተን ወዘተ. ድረስ አሳርን ያያል፡ የባህል ጀግናው ከደሳሳ ጎጆ ወይም ከቤተ መንግስት ወጥቶ፥ ይህን ሁሉ የፈተና ጽዋ ተጎንጭቶ፥ በድል እወጣለሁ ብሎ ጉዞውን አሀዱ የሚለው ደግሞ አንድም ተገዶ፥ አለዚያም ወዶ መሆኑን Campbell ያስረዳሉ። ይህ ግዳጅና ውዴታም ገና ከጥንስሱ ወይም ከመነሻው ጀምሮ በሰዎች ላይ ሃዘኔታን (pathos) ያጠላል። የህይወት ጎዳናው ሁረቱን ቀጥሎ ካለመው ግብ ለመድረስ ሲኳትንም ለሞት የሚዳርጉ ደንቃራዎች፥ ወጥመዶችና አሽከላዎች በአንድነት ተረባርበው ወይም በየተራ ተከታትለው ሲደቀኑበት እንዳች መንፈሳዊ ኃይል ይጋርደዋል። ሆኖም በተቃራኒው ለሚደቀኑበት ደንቀራዎች መናፍስቱ አጋልጠው የሰጡት ወይም ከገጠመው ፈተና ጋር አብረው ያደሙበት እንደሆነ ከተጠመደበት መሰናክል ወይም ከተዘረጋበት ወጥመድ የሚሾልክበት፥ አጋጣሚ አይሉት ቡራኬ፥ እንደ ሰማይ መና ይወርድለታል። ለምሳሌ እሳትን ያገኛል ወይም ሴትን ያስኮበልላል። Campbell እንደሚገልጹት ከሞት የሚያሾልኩ እንዲህ ያሉ በረከቶች (boons) ከእጁ በገቡ ወይም ባጋጠሙት ጊዜ ጀግናው ይበልጥ የአካል

ብርታትንና በውስጡ የህሊና ምጥቀትን ጨምሮ ነው የሚቀዳጀው። ኋላም በህሊና ወይም በተስፋ ምልአት ብቻ ሳይሆን በቅርጽ ለውጥ ጭምር ለድልና ለትንሳዔ ይበቃል (Campbell 1960: 245-246)።

የባህል ጀግኖችን የህይወት ታሪክ በመመርመር፥ የሚያመሳስሏቸውን የጋራ ባህርያት ለማመልከት ከሞከሩት መካከል ከላይ የተጠቀሱት ሎርድ ራግላን (1965 142-149) አንዱ ናቸው። ራግላን የአስራ ስምንት የባህል ጀግኖችን ታሪክ በአጭሩ አስፍረው፥ በመካከላቸው ያለውን ምስስል አመልክተው በበኩላቸው የሚከተሉትን ሃያ ሁለት መመዘኛዎች አቅርበዋል። እነዚህ መመዘኛዎችም:-

(1) ባለታሪኩ ከንጉሣውያን ቤተሰብ ከሆነች እናት ይወለዳል፤ (2) ንጉሥ አባት ይኖረዋል፤ (3) አባቱ ከእናቱ ጋር የስጋ ዝምድና ሊኖረው ይችላል፤ (4) ባለታሪኩ የተጸነሰበት መንገድ ያልተለመደ ይሆናል፤ (5) የአንድ መለኮታዊ ወይም መንፈሳዊ ኃይል ልጅ ነው ተብሎ ይጠረጠራል፤ (6) እንደተወለደም አባቱ ሊገድለው ይሞክራል፤ (7) ግን በአንድ አጋጣሚ ወይም ኃይል በህይወት ይቀጥላል፤ (8) በሩቅ ቦታ በጉዲፈቻ ሊያድግ ይችላል፤ (9) ስለ ህጻንነቱ የሚታወቅ ነገር አይኖርም፤ (10) ሲያድግ ስልጣን ወደሚይዝበት ቦታ ይመለሳል፤ (11) አንድን ንጉሥ ድል ያደርጋል ወይም እንደ ደራጎን ያለ አስፈሪ አውሬን ያሸንፋል፤ (12) የንጉሥ ሚስት ወይም ልጅ ያገባል፤ (13) ይነግሣል፤ (14) ለጥቂት ጊዜ በአንጻራዊ ሰላም ይገዛል፤ (15) ሕግ ያወጣል ወይም ይሰጣል፤ (16) የአማልክትን ፍቅር ያጣል፤ አለዚያም ደግሞ ሕዝብ ይነሳበታል፤ (17) ከስልጣን ይወገዳል፤ (18) አሳዛኝ ወይም ምስጢር የከበበው የሞት ፅዋን ይጎነጫል፤ (19) ሞቱም ኮረብታ ወይም ተራራ ላይ ይሆናል፤ (20) ወራሽ ልጅ አይኖረውም፤ (21) አስከሬኑም አይቀበርም፤ (22) የኋላ ኋላ ግን መንፈሱ ይመለክበታል (Raglan 1965፥ 145)።

እንግዲህ ከዚህ በላይ በአጭሩ ከሰፈሩት ሀሳቦች ተነስተን የኙዋው ኦቴኖ የህይወት ታሪክ፥ የድርጊት ኃይል፥ ደረጃና ዕጣ ምን እንደሚመስል ለመመልከት እንሞክራለን። ትንተናውን በሚነገርበት ባህላዊና ማህበራዊ አውዶች መረዳት ይቻል ዘንድ የኙዋዎች እምነት ምን ይመስላል? የሚለውን በቅድሚያ ማየት አስፈላጊ ይሆናል። ስለዚህ ኙዋዎች ስለ ውጭው ዓለምና ስለ ራሳቸው በአጠቃላይም ስለ ሰው ልጅ ያላቸውን አመለካከት፥ እምነትና አስተያየት፥ እንዲሁም ስለ ህይወት የሚሰጡትን ትርጓሜ እንደሚከተለው በአጭሩ እንመለከታለን።

3. አኙዋዎችና እምነታቸው

አኙዋዎች ስለ ዓለም አፈጣጠር፥ ስለ ሰው ልጅ አመጣጥና ምንነት በሚሰጡት ትርጓሜ መሰረት የሰው ልጅ ሁለት ዓይነት ሆኖ ይገኛል። አንደኛው የሰው ዓይነት "ዳኖ" (*dänho*) ይባላል፤ ዳኖ "ንጹህ፥ ዕውነተኛ የሆነ የሰው ልጅ" (*pure human being*) ማለት ነው። ሁለተኛው የሰው ዓይነት ደግሞ "ፓ-ዳኖ" (*pa-dänho*) የሚባለው ሲሆን በአኙዋዎች አተረጓጎም "ንጹህ ያልሆነ፥ በባህርይውም በድርጊቱም የጥፋት፥ የሞት፥ የህመምና የስቃይ ምንጭ፥ ሰውን የሚጎዳ መንፈስ በውስጡ ተጣብቶት የሚኖር" (*impure human being*) እንደ ማለት ነው። ከዚህ

የተነሳ "ዳኖ" "ፓ-ዳኖ"ን እጅግ በጣም ይፈራል፣ ወይም አንዱ ሌላውን ይጻረራል፣ "ዳኖ" እና "ፓ-ዳኖ" አጥፊና ጠፊ በመሆናቸው "ዳኖ" ከ"ፓ- ዳኖ" (*pa-dänho*) ራስ -ን ለመጠበቅ እነሆ የመከላከያ ስልት ፈጥሮ ዛሬም በህብረተሰቡ ውስጥ ሲሰራበት የሚታይ ይመስላል። አኙዋዎች ስለ ሰው ልጅ ያላቸው ይህ አይነቱ የቆየ አመለካከትና እምነት ከፈጣሪ ባህርያት ጋር የተቆራኘ ሆኖ ነው የሚገኘው።

በአኙዋዎች አተያይ አለምን ፈጥሮ ህይወትን የዘራ አንድ ሰማያዊ ኃይል (high god) አለ። እሱም "ጆክ" (Jwøk) ይባላል። "ጆክ" የሚለው ቃል እግዚአብሄር እንደ ማለት ሲሆን፥ የተቃርኖ ባህርይ አለው። አንድም ሁለትም ነው። በሁለትነቱ "*ጆኩ ኚንጋላብዎ*" (*Jwøk -ñyingalabwøø*) እና "*ጆኩ-ዱጉ-ኚንጋላብዎ*" (*Jwøk-dugu-ñyingalabwøø*) ተብሎ ይጠቀሳል። ቀዳሚው ባህርይ ዓለምን ፈጥሮ የዘራባት ህይወት ያለ ምንም ህመምና ሞት፥ ያለ ሳንክ፥ ዘለአለማዊ ሆና እንድትቀጥልና እንድትኖር ያደርጋል። ሁለተኛው፥ ተቃራኒው ባህርይ--"*ጆኩ-ዱጉ-ኚንጋላብዎ*"--ግን አፍራሽ፥ ዕኩይ ነው ተብሎ ይታመናል። የተፈጥሮ ሕግን ያፋልሳል። ፍጥረትን ያጠፋል። ህይወትን ይቀጥፋል። መብረቅ፥ ማዕበል፥ እሳተ ገሞራ ያወርዳል። በአጠቃላይ የሰው ልጅ የሚገጥመው ፈተና፥ ስቃይ፥ ሞትና ፍዳ ሁሉ ከ"*ጆኩ-ዱጉ-ኚንጋላብዎ*" ባህርይ የሚመነጭ ተግባር ነው ተብሎ ይታመናል። ጆክ እነዚህን ተቃራኒ ባህርያት በዋህድነት ይዞ በሰማይ እየኖረ፥ በክፉም ይሁን በበጎ ገጽታው ፈቃዱን የሚፈጽሙ ምድራዊ ወኪሎች (agents/ mediators) አሉት። ከወኪሎቹ መካከልም የሰው ልጅ አንዱ ነው። በእምነቱ. መሠረት ሁለቱም የ"ጆክ" ባህርያት ሴት ወንድ ሳይሉ የሰው ልጆችን "በሚስትነት" ይዋሰቧቸዋል፣ ያገቧቸዋል፣ አብረዋቸውም ይፈጠራሉ። ስለሆነም "*ጆኩ-ዱጉ-ኚንጋላብዎ*" ያገባቸው ሰዎች የህማም ዓይነቶችን የመፍጠር፥ ሰውን የመግደል፥ የማሳበድ ኃይል አላቸው ተብሎ ይታመናል። እንዲህ ያሉት ዓይነቱ ሰዎች የመርዝ ብልቃጦች ወይም የሞት መያዣ ሰገባዎች (ማስኮች) ናቸው። እነዚህ ፍጡራን በጥቅል "ቺ-ጆክ" (ci-jwøk) ተብለው ይጠራሉ። "ቺ-ጆክ" ማለት የ "*ጆክ-ዱጉ-ኚንጋላብዎ*" ሚስት፥ ወኪል፥ ልጅ ማለት ነው። "ቺ-ጆክ" በቅርጽ የሰው ልጅ ይምሰል እንጂ እውነተኛ ሰው ሊባል ከቶ አይችልም፣ ስለዚህ "ፓ-ዳኖ" ነው። በአኙዋዎች እምነት "ፓ-ዳኖ" የሚያሰኘው አንዱ ዋነኛ ምክንያት፥ እንደተገለጸው፥ "ቺ-ጆክነት" ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ በእምነቱ መሠረት አኙዋዎች ራሳቸው፥ ከፍርሃትና ከስጋት ለመከላከል "ቺ-ጆክ"ን ወይም "ፓ-ዳኖ"ን የማራቂያ፥ ነው። ደግሞ የማስወገጃ የቆየ ልማድን መጠቀሚያ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፥ የ"ቺ-ጆ‌ኬውሁ ከሳች ምልክቶችንም ለይተው እንደሚያውቁና ዕውቀቱንም በተግባር እንደሚያውሉ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ድርጊት ወይም ማህበራዊ ጠባይ አለ።

ለምሳሌ የተፈጥሮ ግርዝነት ከ"ቺ-ጆክ" ከሳች ምልክቶች አንዱ ተደርጎ ይታያል። ባህሉ የግርዘትን ተግባር ብቻ ሳይሆን፣ በተፈጥሮ ግርዝ ሆኖ መወለድንም አይቀበልም። ምልክቱ ከህብረተሰቡ ጋር አያዋህድም። ከዚህ አኳያ "የማርያም ግርዝ" ተብሎ የሚጠቀሰው የተፈጥሮ ግርዝ በአኙዋዎች ዘንድ የ"*ጆኩ-ዱጉ-ኚንጋላብዎ* ሚስት" ወይም "ዲቃላ" (ñyi- ci- jwøk) መሆኑን መረዳት እንችላለን። ከዚህ የተነሳም በአኙዋ ህብረተሰብ ውስጥ ልደት በፍርሃትና በደስታ

የተዋጠ ክስተት ሆኖ ይገኛል። በተቃራኒው ሞት በኡኙዋዎች ዘንድ ሞት አይደለም፤ የዘላለማዊ ህይወት ሌላ ምዕራፍ እንጂ። ከዚህ የተነሳ፥ ብዙውን ጊዜ፥ በኡኙዋዎች ዘንድ አይለቀስም። የሚለቀሰው ዋቶንግ (a member of the lowest section of the society due to curse) የሞተ እንደሆነ ነው። በኡኙዋዎች እምነት ዋቶንግ ይሞታል፤ ወይም፤ በሌላ አባባል፤ ነፍሱ ወደ ውሃ አትመለስም። ወይም፥ *የዋቶንግ ነፍስ* ቅርጽ ቀይራ፥ ቶተም ሆና፥ እርግማን እንዳልወረደባቸው እንደ ሌሎቹ ኡኙዋዎች መናፍስት ከሞት በኋላ በህይወት ትመጣለች ተብሎ አትታሰብም-። ከዚህ ውጭ በኡኙዋ ውስጥ ሰው ሞተ ተብሎ አይታዘንም። ምክንያቱም "በኡኙዋዎች እምነት ሞት ተፈጥሯዊ አይደለም። ሞትን የሚያስከትሉ ችግሮች፥ አንድም ች-ጆክ፥ አለዚያም ደግሞ አሸኒ (እርግማን) ናቸውና" (Perner 1991:20)።

4. የኦቴኖ አጭር ታሪክና ትንተና*

4.1 አጭር ታሪክ

(1) ኦቴኖ የንጉሣውያን፥ የኝያ (ňyieya) ዘር ነው፤ እናቱ የንጉሣውያን ቤተሰብ አባል ነች፤ (2) ስለአባቱ ግን የሚታወቅ ታሪክ የለም፤ (3) ጽንሰቱ ከአንድ ሰማያዊ ኃይል ጋር በመያያዝ ምስጢር የተሞላበት ሆኖ ይገኛል፤ (4) የጆክ-ዱት-ኝንጋላብዎ ዲቃላ በመሆኑ በተፈጥሮ ግርዝ፥ መልኩ አስቀያሚና ቁመቱ ስንዝር የሚያክል፥ ድንክ፥ ነው፤ (5) በዚህም ቤተሰቡ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ ሕብረተሰቡ ወይም ባህሉ ሊያስወግደው ይሻል፤ (6) በህይወት ለመቀጠሉ ምክንያት መሆኑ በቀጥታ ባይገለጽም ከንጉሡ ልጅ ከጊሎ ጋር በአንድ ቀንና ስሰት ተወልዷል፤ በባህሉ መሠረት ለጊሎ ህልውና ሲባል ኦቴኖ በህይወት እንዲቀጥል ተደርጓል፤ (7) ከህብረተሰቡ ተገልሎ አድጓል፤ (8) የህጻንነት ዘመኑ በሰ ፊው ይታወቃል፤ (9) የገድል ጥሪውን ይቀበላል፤ ወደ ደን ይገባል፤ (10) በዚህ ዓለም ብቸኛ አለኝታ የሆነውን ንጉሥ ጊሎን (የአክስቱን ልጅ) ይገድላል፤ (11) ከዚያም የንጉሥ ጊሎን ሚስቶች ይወርሳል፤ (12) ይነግሣል፤ (13) የሕዝብ ቁጣ ይባባስበታል፤ (14) ለመጀመሪያ ጊዜ ከአፈር አንጥሮ "ደም" (dèm) የተባለ የብረት ጦር ይሰራል፤ ጦርነትም ከሕዝቡ ጋር ይገጥማል፤ (15) ለጊዜው ድል ያደርጋል፤ (16) ቆይቶ ግን ንጉሥ ጊሎን ያለ ምንም ጥፋት የገደለው መሆኑ ሲቆጠጽለት አሰቃቂ በሆነ ሃዘን ልቡ ይሰበራል፤ ሃዘኑን ለመቋቋም ሲል ለመጀመሪያ ጊዜ "ቶም" እና "ክራር" የተባሉ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ይሠራል፤ (17) በሃዘን ላይ እንደወደቀ ሕዝቡ ኦቴኖ የሰራውን «ደም» የተባለውን የብረት ጦር መሥራት በመቻሉ ጦርነት ተቀስቅሶ ኦቴኖን ድል ያደርጋል፤ አከላቱንም ቆራርጦ ይጥላል፤ (18) የተቆራረጠው አከላቱ በአንድ መንፈሳዊ ኃይል እንደ ገና ተገጣጥሞ ወደ እሳት ዘንዶነት በመቀየር አገረ ኡኙዋን እየተዘዋወረ በቋያ እሳት ይለበልባል፤ (19) በዚህ ጊዜ የጊሎ እናት (አካንጎ) የሰው ዘር ይተርፍ ዘንድ ትማጸነዋለች፤

---

*ለግንዛቤ ያህል ሙሉ ትረካው በአባሪነት ቀርቧል

(20) እሱም ምህረት አድርጎ እንደ ገና ወደ ቀድሞ ቅርጹ ይመለሳል፣ (21) አካኑን በቅል አድርጋ ወንዝ ላይ እንድትጥለው ይጠይቃታል፣ እሷም ከቅል ውስጥ ከትታ ኦፔኖ (ባሮ) ወንዝ ላይ ትጥለዋለች፣ ወደ ውሃ ይመለሳል፣ (22) ከዘመናት በኋላ ግን ወደ "ፈረንጅነት" ተቀይሮ መጣ በመባል፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሽብር ይፈጠራል፣ ዛሬም ኦቴኖ በህይወት አለ ተብሎ ይታመናል።

4.2 ትንተና:-

ከታሪኩ እንደምንመለከተው፣ ኦቴኖ የተወለደው በተፈጥሮ ግርዝ፥ መልኩ ለአይን የሚያስጠላ ቁመቱም እንደዚሁ እጅግ በጣም አጭር ሆኖ ነው። ይህ ደግሞ ከህብረተሰቡ እምነት አኳያ የጥፋት ምልክት በመሆኑ በእንግድነት የመጣበት ዓለም የሚቀበለው በእልልታ ሳይሆን በድንጋጤ፥ በፍርሃትና በስጋት ተውጦ ነው። ከዚህ የተነሳ በህብረተሰቡ እውቀትና በህጻኑ ኦቴኖ መካከል ቀውስ ይፈጠራል። ህብረተሰቡ ባለው እውቀት እንደ ኦቴኖ የዕኩይ መንፈስ ምኩራብ ናቸው ብሎ የሚያያቸውን ሁሉ አስወግዶ ከተፈጠረበት ፍርሃትና ስጋት ነፃ ሆኖ ደህንነቱን ማረጋገጥ ነው። በሌላ በኩል ህጻኑ ኦቴኖ የመጣበትን ዓለም ስጋት ላይ መጣሉን ሊገነዘብ በሚችልበት የዕድሜ ደረጃ ላይ አይገኝም። ስለዚህ የጥላቻ ፅዋ ለተወሰነ ጊዜ በደመነፍስ፣ ሳይታወቀው፣ እየጨለጠ እንዲኖር፥ ሕልውናውም በአደጋ እንዲከበብ ሲገደድ እንመለከታለን።

ሌሎቹ የባህል ጀግኖች ሲገጥማቸው እንደሚታየው የልደቱን ቅጽበት ተከትሎ የመጣው ይህ ዓይነቱ አደጋ በህፃኑ ኦቴኖ ላይ የሚጋረጠው በግላዊ እምነት ተመስርቶ አይደለም፣ በአጠቃላዩ በህብረተሰቡ በቆየ አስተሳሰብ፥ አመለካከትና እምነት ላይ እንጂ። በባህሉ መሠረት፥ ኦቴኖ "ች-ጆክ" ወይም "ፓ-ዳኖ" ነው። በመሆኑም፣ ባህሉ ሊያስወግደው ይችላል። ነገር ግን Jung እና ኬረኒ (1963: 87) እንደሚገልጹት እንደ ኦቴኖ ላሉ ሕፃናት ተፈጥሮ ክንፏን ትዘረጋለች፣

> Abandonment, exposure, danger, etc. are all elaborations of the 'child's' insignificant beginnings and of its mysterious and miraculous birth. . . . Nothing in all the world welcomes this new birth, although it is the most precious fruit of Mother Nature herself, the most pregnant with the fruit, signifying a higher stage of self-realization. That is why Nature, the world of the instnicts, takes the 'child' under its wings: it is nourished or protected by animals.

ኦቴኖን በህይወት እንዲቀጥል ያደረጉት አከናፍ በታሪኩ ውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድ ተገልጾዋል። ለምሳሌ፥ ኦቴኖ ከንጉሡ ልጅ፥ ከጊሎ፥ ጋር የተወለደው በአንድ ቀንና ሰዐት መሆኑ በህይወት እንዲቀጥል ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ይሆናል። በአኙዋዎች ዘንድ በአንድ ቀን ወይም ሰሞን መወለድ «ቲያንግ» ይባላል:: ይህም ጥልቅ ትርጉም ይሰጠዋል። በመሆኑም፥ ኦቴኖና ጉሎ «ቲያንግ» ናቸው:: ኦቴኖን መግደል በአንድ ቀን አብሮት የተወለደውን ንጉሥ ጊሎን እንደ መግደል•

ይቆጠራል። ስለዚህ፡ በአዥዋዎች ምናባዊ የፈጠራ መንገድ የጊሎ አብሮ መወለድ የቀውሱ ገላጋይ (mediator) ሆኖ መቅረቡን ያሳያል። ይሁን እንጂ፡ ኦቴኖ በማህበረሰቡ ከመገለል ሊያመልጥ አለመቻሉን ቀጥሎ ከሰፈረው ከትረካው ክፍል መገንዘብ እንችላለን፥

> ኦቴኖ ሲወለድ ግርዝ፥ ከዚያም በተጨማሪ ስንዝር የሚያህል ኦጭር በመሆኑ ሁሉም ሰው ጠላው። እሱ የጠጣበትን ዕቃ ሌላ ሰው አይጠጣበትም። እሱ የበላበትን ዕቃ ማንም ሰው አይበላበትም። እሱ የነካውን ማንኛውንም ነገር ሌላ ሰው አይነካም። ኦቴኖ የነካው እህል እሩቅ ቦታ ይደፋል። ጸሐይ እንዲመታው የተሰጣ ዘንጋዳ፡ ማሽላ፡ በቆሎ፡ ክክ፥ ዱቄት ወይም የአሳ ቋንጣ ኦቴኖ ተራምዶት ካለፈ ውሃ ውስጥ ይጣላል። ከእሱ ጋር ሰው አብሮት አይተኛም። የሚነካው፥ የሚቀርበው ሰው አልነበረም። ሴቶች ገና ከሩቅ ሲያዩት "ች-ጀክ" እያሉ የያዙትን ዕቃ እየጣሉ በርግገው ይሸሹ ነበር።

ኦቴኖ በህጻንነቱ በዚህ ሁኔታ ከህብረተሰቡ ተገልሎ ሲኖር በተወለደበት ቀን የተወለደው የአክስቱ የአካንጎ ልጅ ጊሎ ብቻ ያነጋግረው፥ ይቀርበው፥ ይወደውና ያፈቅረው እንደ ነበር ከታሪኩ ጨምረን እንረዳለን፥

> ኦቴኖን ሰው ሁሉ ጠልቶት ብቻውን ሲኖር ከቤተሰቡ መካከል ይወደው የነበር የኘያው-- የንጉሱ-- ልጅ ጊሎ ብቻ ነበር። ጊሎ የእናቱ የእህት ልጅ ነው። ጊሎ ኦቴኖን እንዳይቀርበው፥ እንዳይነካውና አብሮት እንዳይሄድ ቢነገረውም እሽ ብሎ አይቀበልም፤ አይሰማም ነበር። ኦቴኖም ከጊሎ ሌላ ማንም ስለማያቀርበው ከጊሎ መለየትን ፈጽሞ አይፈልግም ነበር።

ኦቴኖ በቁመት ባይጨምርም በዕድሜ እየበሰለ በሄደ መጠን በምን ምክንያት ሰው ሁሉ ሊጠላው፥ ህብረተሰቡም ለምን ሊያገለው እንደቻለ ለመረዳት ራሱን መጠየቅ ይጀምራል። በእርግጥም *"The urge and compulsion of self-realization is a law of nature and thus of invincible power, even though its effect, at the start is insignificant and improbable" (Jung and Kerenyi, 1963, 89)*። እነ Jung አንድ የባህል ጀግና ወደ ውስጥ ራሱን፥ ወደ ውጭ ሕብረተሰቡን ለመመርመር ብስለት እያገኘ ሲመጣ የራሱን ነጻነት ለማረጋገጥ እንደሚሻና እንደሚነሳሳም ጨምረው ያስገነዝባሉ። ዕጣው ለባህል ጀግንነት የተቆረጠ እንደ ኦቴኖ ያለ ህጻን በዚህ ደረጃ ላይ ሲገኝ ህብረተሰቡ ከያዘው ዕውቀት አንጻር የሚኖረውን ልዩነት በጉልህ የሚያመለክት የአስተሳሰብ ብስለት ያዳብራል። ይህን የአስተሳሰብ ደረጃም Campbell "የገድል ጥሪ" (a call to adventure) በማለት ይገልጸዋል። በዚህ ብስለትና ደረጃ ላይ ነው የህብረተሰብ ዕውቀትና የጀግናው ዕውቀት ልዩነት ይበልጥ የሚከረው፡ የጀግናው ዕውቀት፥ አእምሮ፥ ይመጥቃል፤ በተቃራኒውም ከእሱ እይታ አንጻር የህብረተሰቡ የወል አመለካከት ይዘቅጣል። ይሁን እንጂ Campbell እንደሚገልፁት፥ ጀግናው ወደማያውቀው አቅጣጫ፥ "ወደ ጨለማ (darkness)፡ ማለትም ወደ ምድረ በዳ፥ ወደ ደን፥ ወደ ሃይቅና ረግረግ፥ ወደ ባዕድ አገር፡ ወዘተ. እንዲገባ ይገደዳል (1960: 49፥ 58፥ 79)።

ኦቴኖም ይህን አቅጣጫ ተከትሎ ሲኳትን እናያለን። በመጀመሪያ ራሱን እንዲፈልግ፥ ህብረተሰቡንም እንዲያውቅ ይገደዳል። ያለ ማቅማማት ድርጊቱን

እንዲያፋጥን የሚያግዘውም ለህልውናው መቀጠል ምክንያት ከሆነው ከጊሎ አንጻር በተቃራኒ የመቀረጹ ሁኔታ ነው። ይህንም ከታሪኩ ጠቅሰን እንመልከት፤

> ጊሎ እጅግ በጣም የሚያምር ልጅ ነበረ።...ቁመቱ ረጅም፥ ሰውነቱ ወፍራም፥ አይኑ ዛጎል የሚመስል ነበር። ቁመቱ መልኩ የሚያምር ስለነበር ልጃገረዶች ጊሎን ሲያዩት ይከቡት ነበር። ሴቶች ከጊሎ ተለይተው መሄድ ሞት መስሎ ይታያቸው ነበር። ጊሎን በመልኩና በቁመናው ማማር ሴቶቹ ብቻ ሳይሆኑ የሚወደው ሁሉም ነበር።

ባንድ በኩል ኦቴኖ፥ ድንክ፥ እጅግ በጣም አጭር፥ ግርዝና በመልኩም እጅግ በጣም አስቀያሚ በመሆኑ ህብረተሰቡ ሲያገለው፥ የሚበላ የሚጠጣ ነገር እንዳይነካና፥ ከሰውም እንዳይቀርብ ሲከለክለው፥ ሴቶች ባዩት ቁጥር ተኩላ እንዳየ የፍየል መንጋ "ች-ጀክ" እያሉ ሲሸሹትና ሲበረግጉ በሌላ በኩል ጊሎ በውበት የታደለ ሆኖ እናያለን። ግን እንደ ኦቴኖ ብልህና አዋቂ ሆኖ በታሪኩ ውስጥ አይቀርብም፤ ጊሎ ፍሬ አልባ ነው። ጊሎ ክፉን ከደግ ለይቶ አያውቅም፤ ነገር ግን ሰዎች በተለይም ሴቶች ይወዱታል። ከዚህ በተቃራኒ ኦቴኖ የጥበብ፥ የፈጠራና የዕውቀት ምንጭ ሆኖ ተቀርጿል። በኦቴኖ ልቡና ውስጥ የአመጽ መንፈስ የሚጠነስሱት በእርሱና በተቃራኒው ባህርያት መካከል የምናገኛቸው ልዩነቶች ይሆናሉ። ህብረተሰቡ ስለ "ች-ጀክ" የሚሰጠውን ትርጉምና የሚያሳየውን ምግባር ከራሱ ህልውናና ዕጣ ጋር በማቆራኘት ይገነዘባል። Okpewho *(1975:10)* "ጀግና በዝምታ ተውጦ ነዶ እስከሚጠፋ አይጠብቅም። ክብሩን የሚያረጋግጥበት አጋጣሚ በመሻት በጀግንነት ይፋለማል እንጂ" በማለት እንደሚገልጹት ኦቴኖም "ፓ-ዳኖ" እና የእኩይ መንፈስ ምኩራብ፥ ወይም "ች-ጀክ" አለመሆኑን ለማረጋገጥ አመጽን ሳይወድ በግድ በልቡ ይጠነስሳል። በዚህ የህሊና ዝግጅት ሂደት ውስጥ እንዳለ በተቃራኒ የቆመው ጊሎ ንጉሥ ሆኖ በህዝቡ ዘንድ ይመረጣል። ኦቴኖ "ች-ጀክ"፥ "ፓ-ዳኖ" ነው ተብሎ ባይጣል፥ ባይጠላ፥ ባይናቅ፥ ባህሉ በሚፈቅደው በ"ኘያ" ደንብ መሠረት የንጉሥ ዘር፥ ከዚያም በላይ ብልህና አዋቂ በመሆኑ በሥርዓተ ንግሡ *(rony)* ላይ መገኘት ነበረበት። ግን ኦቴኖ "ሰው ስላልሆነ" ከዙፋን (ውሎ) ላይ ለመቀመጥ መታጨቱ ቀርቶ ከሰው ጋር የሚገናኝበት ዕድል እንኳን ይነፈገዋል።

እነዚህ ሁኔታዎች ሁሉ ተዳምረው ኦቴኖን ራሱን ወደ ውስጥ እንዲያይ ያስገድዱታል። እውነተኛ ሰው እንጂ በሰው ላይ ህመም፥ ስቃይና ሞትን የሚያስከትል "ፓ-ዳኖ" አለመሆኑን ለማረጋገጥ በአስተሳሰብ ያበስሉታል። እያደር፥ ቀስ በቀስ፥ ያበስሉታል፤ ይገፋፉታል፤ ወደ ድርጊትም እንዲያመራ ያነሳሱታል። በመጨረሻም የጉዞው አህዱ በዚህ አለም በብቸኝነት ፍቅር ያሳየው የነበረውን ለህይወቱ መቀጠልም ጸር በሆነው ባህል ውስጥ ለህልውናው መቀጠል ምክንያት የሆነውን፥ በተወለደበት ቀንና ሰዓት አብሮት የተወለደውን ንጉሥ ጊሎን መግደል፥ ሕልሙም ስልጣን ይዞ በኮነነው ባህል ላይ የበላይነትን መቀዳጀት ይሆናል። ይህን ሕልሙን እውን በማድረግ በእርሱ አይን ዘቅጦ የሚታየውን "ች-ጀክነት" ሽሮ እውነተኛ የሰው ልጅነቱን በማረጋገጥ ይልቁንም እርሱን ሲያዩ ይበረግጉና በአንጻሩ ደግሞ ጊሎን ሲያዩ ይከቡት የነበሩትን ሴቶች መውረስ አላማው ይሆናሉ። በመሆኑም ገድሉን ይፈጽም ዘንድ በጨለማ ወደ ደን ያመራል። ይህን ከታሪኩ ክፍል እንደሚከተለው ብንመለከት ይበልጥ ልንረዳ እንችላለን።

ኦቴኖ ንጉሥ ጊሎን "ወደ አደን እንሂድ፤ ለብዙ ጊዜ ሥጋ አልበላንም፤ ሥጋ ያስፈልገናል፤ አደን ብንሄድ ምን ይመስልሃል?" ብሎ ጠየቀው። ንጉሥ ጊሎም በኦቴኖ ሃሳብ ተስማማ። ኦቴኖ በሃሳቡ መስማማቱን እንዳወቀ "ሌላ ሰው አብሮን መሄድና የምንሄድበትን አቅጣጫ ማወቅ አይኖርበትም። ከእኔ ጋር ለአደን መሄድህን ማንም ሰው ማወቅ የለበትም። ለአደን ልሄድ ነው ካልክ ሰው ይከተልሃል። ስለዚህ ብቻህን ውጣ" አለው። ንጉሥ ጊሎም "እሺ! በሌሊት እንሄዳለን" በማለት ተስማማ። ከዚህ በኋላ ኦቴኖ "ከእኩለ ሌሊት በኋላ ሰው ሁሉ ሲተኛ ሳትታይ ውጣ" አለውና የሚገናኙበትን ቦታ ወሰኑ። ቦታው ከሚኖሩበት አገር የራቀ ነበረ። ለመገናኘት የተነጋገሩትም ከትልቅ ዋርካ ሥር ነበር። በመጨረሻም "ቀድሞ የደረሰ ከዋርካው ሥር ቁጭ ብሎ ይጠብቅ" ተባብለው ተለያዩ። በዚያ ዘመን እንደ ዛሬው ከብረት የተሠራ ጦር አልነበረም። ጊሎም ኦቴኖም የያዙት ከዝሆን ጥርስና ከአጥንት የተሰራ ጦር ነበር።... እንደተለያዩ ኦቴኖ ወደ ተቀጣጠሩበት ቦታ ሄደ። ጊሎም እንደዚሁ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ሰው ሁሉ ሲተኛ ከቤተ-መንግስቱ (ከቡራው) ሳይታይ ሾልኮ በመውጣት ውሻውን አስከትሎ ሄደ።

ከታሪኩ እንደምንረዳው ከተቀጣጠሩበት ቦታ ቀድሞ የሚደርሰው ኦቴኖ ከዋርካው ሥር ቁጭ ብሎ መጠበቅ ሳይሆን ከዋርካው ቁንጮ ወጥቶ ይቀመጣል። ይህ የኦቴኖን አላማ ስኬታማነት ወይም የህልሙን ፍቾ የሚፈነጥቅ ድርጊት ነው ማለት እንችላለን። በመሆኑም ንጉሥ ጊሎ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ከቡራው እንዲወጣ ይገደዳል። ጦሩን ይዞ ውሻውን አስከትሎ ከሄደ በኂላ ከዋርካው ስር ይቀመጣል። እናም ድንኩ ኦቴኖ እንደ ቀድሞው ወደ ሰማይ አቃንቶ ሳይሆን ጊሎን ከላይ ወደ ታች አቆልቁሎ ለማየት ይበቃል። ከዚያም ራሱን በጦር ይወጋውና ይገድለዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በታሪኩ ውስጥ የጊሎ ውሻ የተሰጠውን ሚናና የሚያመለክተውን ትርጉም ልብ ማለት ያሻል። ንጉሥ ጊሎ በጦር መወጋቱን እንዳየ ውሻው ከደሙ ላይ ተንከባሎ እያለቀሰ ወደ ሰፈር በመሮጥ ከቡራው፥ ከቤተ-መንግስቱ፥ ከደረሰ በኋላ ወዲያ ወዲህ እየተቁነጠነጠ ማልቀስና ማዘኑን ትረካው ይነግራል። በዚህ ጊዜ የንጉሡ ጀቡራዎችና ዋዲዎች፥ ዘቦች፥ እንዲሁም እናቱ አካንጎና ሚስቶቹ የውሻውን ጭንቀት በሃዘኔታ ቢመለከቱም ምክንያቱ ወዲያው ሊገለጽላቸው አልቻለም:: ሆኖም ቆይቶ ከቡራው ውስጥ ከተሰበሰበውና የውሻውን አሳዛኝ ሁኔታ ከሚመለከተው ሰው መካከል ንጉሥ ጊሎ አለመኖሩን ለመገንዘብ ምክንያት ይሆናል። ስለዚህ አካንጎ ደም የተቀባው ውሻ ስለሚያዝንበትና ስለሚያለቅስበት ሁኔታ ንጉስ ጊሎን ልትነግረው ወደ መኝታ ክፍሉ ትሄዳለች። ጊሎን ግን ታጣዋለች። በዚህ ሁኔታ የውሻው ለቅሶ የጊሎን መጥፋት ይጠቁማል። በመሆኑም ሰው ሁሉ በአካባቢው ንጉስ ጊሎን ለመፈለግ ሲሰማራ እናያለን። በታሪኩ ውስጥ ውሻው መልዕክት አድራሽ ብቻ ሳይሆን እውነት ፈንጣቂ ሆኖ ቀርቧል። ይሁን እንጂ ለጊዜው ጊሎ ሊገኝ ባለመቻሉ "ቡል" (ነጋሪት) ይመታል። የአገሩ ህዝብም ድምድምታውን እንደሰማ በድንጋጤ በቡራው ዙሪያ ይሰበሰባል። በአኙዋዎች ዘንድ ቡል በትንሽ በትልቁ ችግር አይመታም። ንጉሥ ሲሞት፥ አገር ሲወረር ወይም ሥርዓተ በዓል ሲከበር እንጂ። በመሆኑም ንጉሥ ጊሎ ከቡራው መጥፋቱ በውሻው አማካይነት እንደታወቀ ቡል ሊመታ መቻሉን እንገነዘባለን። ጊሎ

ካለ አንዳች ችግር ሊሰወር እንዳልቻለ በመገንዘብ በአገሩ ጭንቀት ሰፍኖ እንደነበርም ኦቴኖ ወደ ቡራው ይመለሳል። የጊሎን ዙፋንና ሚስቶቹን መውረሱንም ያውጃል።

በአንድ በኩል ጊሎን በመፈለግ ላይ የሚገኘው ህዝብ ኦቴኖን የሞትና የህመም፥ የጦርነትና የፍጅት ምንጭ አድርጎ ያየዋል። ስለዚህ ሊያስወግደው ይፈልጋል። በሌላ በኩል ኦቴኖ "ዳኖ" (እውነተኛ ሰው) መሆኑን ለማረጋገጥ ቁንጮ ላይ ወጥቷል። ቀድሞ ይሸሽ የነበረው ሁሉም "ዳኖነቱን" አሜን ብሎ እንዲቀበል ይጥራል። በዚህም ባህሉ ከስሩ ይጎሻል። እምነት፥ አስተሳሰብና ልማድ ይደፈርሳሉ። ስራቱ ይናጋል። ይህ ሁኔታ እንደተፈጠረ አካንጎ የጊሎን መጥፋት፥ ውሻው የተቀባውን ደምና የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ከኦቴኖ አመጽና "ውሎ" (ዙፋን) አወጣጥ ጋር ታቆራኘዋለች። የአገሩ ህዝብም ምስጢሩን በመጨረሻ እንደ እርሷው ይገነዘባል። በመሆኑም በአንድ በኩል ህዝቡ በሌላ በኩል ኦቴኖ ብቻውን ተሰልፈው ጦርነት ይገጥማሉ። በዚህ ላይ፥

> ...ሊጠቀስ የሚገባው ዐቢይ ጉዳይ የባህል ጀግኖች በጦርነት ፈጽሞ ድልን የማይቀዳጁ መሆናቸው ነው። የባህል ጀግኖች ጦርነት ብዙውን ጊዜ የሚገጥሙት ወይም የሚፋለሙት ብቻቸውን ነው። እንደ ታሪክ ጀግኖች ሰራዊት አያስከትቱም፤ የባህል ጀግኖች ሰራዊት አላቸው ቢባል እንኳን አዛዦች ሆነው አይሰለፉም። በእርግጥ ከታሪክ እንደምንረዳው ንጉሶች አዛዥ፥ አዋጊም ሆነው መታየታቸው የታመነ ነው። አንድ የባህል ጀግና ግን በተቃራኒው የጦር አዛዥ ሆኖ .አይታይም። የባህል ጀግና የሚዋጋው ወይም እንደ ደራጎን ካሉ አስፈሪ አራዊት ጋር የሚተናነቀው ብቻውን ነው። ለድል የሚበቃውም በአንድ የጦር አውድማ ወይም ፍልሚያ ነው (Raglan 1965: 153)።

ኦቴኖም ብቻውን ሆኖ ነው ሲፋለም የምናገኘው። ከኋላው ሠራዊት አያስከትልም። በእርግጥ ችሎታውን፥ ጥበቡንና ዕውቀቱን በመጠቀም ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ድል ሲቀዳጅ እናያለን። ኦቴኖ ከህብረተሰቡ የባህል ደረጃ ቀድሞ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን ለመጀመሪያ ጊዜ ብረት ከአፈር አንጥሮና አቅልጦ "ደም" የተባለ ጦር ሰርቶ መዋጋት በመቻሉ ነው ለጊዜያዊ ድል ሊበቃ የሚችለው። በመሆኑም ስልጣን ላይ፥ ዙፋን (ውሎ) ላይ ይቀመጣል፤

በአንድ በኩል ባህሉ ደፍርሶና የህብረተሰቡ እምነት ተናግቶ የህዝቡ ስሜት ውስጥ ለውስጥ ይብላላል። በሌላ በኩል ራሱን ለማረጋገጥ መብቃቱ በውስጡ የሚሰማው ኦቴኖ የዕጣውን ሁረት አሃዱ ብሎ ሲጀምር በዚህ ዓለም ውስጥ እንደ ሰው ይቆጥረውና እውነተኛ ፍቅር ያሳየው የነበረውን ለህልውናውም ምክንያት የሆነውን ንጉሥ ጊሎን በመግደል ይቅር የማይለው ጥፋት መፈጸሙን ይገነዘባል። በከባድ ጸጸት ላይም ይወድቃል። ይህን ጉዳይ በሚመከት Campbell (1960) የሚከተለውን ይላሉ፤

> *The battlefield is symbolic of the field of life, where every creature lives on the death of the other. A realization of the inevitable guilt of life may so sicken the heart that...one may refuse to go on with it*

ኦቴኖም የሚገጥመው ይህ ሁኔታ ነው። ስለዚህ ሃዘኑን መሸከም ያቅተዋል። በመሆኑም ጊሎን ይቅርታ ለመለመን ሌት ተቀን ማንጎራጎሩን ይቀጥላል። የብረት ጦር፥ ዴም፥ ሰርቶ እምነትንና ልማድን ድል ሊያደርግና ዕውነተኛ ሰው መሆኑን በህብረተሰቡ ዘንድ ለማረጋገጥ "የቻለውን" ያህል ግጥም እየደረደረ በእንጉርጉሮ ሙሾ በማውረድ ብቻ ልቡን የሚበረብረውን ሃዘን ድል መንሳት ያቅተዋል። ይህም ጊሎን ለማውሳት፥ ለማወደስና ይቅርታ ለመለመን በጸጸት የተጥለቀለቀ ስሜቱ ቶምና ክራር የተባሉ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመፍጠር እንዳስገደደው ከታሪኩ እንገነዘባለን።

ኦቴኖ ድልን የተቀዳጀበት ጊዜ የሃዘንና የጨለማ ዘመን ሆኖበት እንዳለ ሌላ ፈተና ይገጥመዋል። ይኸውም መወገዱን አጥብቆ በሚሻው ባህል ዘንድ የዘመናዊ ጦር፥ የዴም አሰራር፥ ስርጸት የማግኘቱ ጉዳይ ይሆናል። እሱ የፈለሰፈውን "ዴም"፥ የብረት ጦር፥ ህዝቡ በገፍ ለማምረት በመብቃቱ በውሎው፥ በዙፋኑ፥ ሥር የሚገኘው ህዝብ ኦቴኖን በመውጋትና ድል በማድረግ አከላቱን ቆራርጦ ይጥለዋል። ይሁን እንጂ የዕጣው መዘውራዊ ሁረት ወደ ትንሳዔ ታመራለች። የተቆራረጡት የሰውነቱ ክፍሎች በአንዳች ተአምራዊ ኃይል ተገጣጥመው ነፍስ ይዘራሉ። የጥርጣሬውን መንፈስ በማጉላትና ንግሩን በመፍታት ራሱ የሰው ከአንገቱ በታች ደግሞ የዘንዶ ቅርጽ ይይዛል። ታሪኩ እንደሚነግረን ዘንዶው የማይጠፋ የእሳት ነበልባል ይሆናል። አገሪ አኙዋንም እየተዘዋወረ በእሳት ቋያ ያቃጥላታል። ይህ በጮርቃው ፊጦን ምክንያት የተፈጠረውን የእናት ምድርን ልመና ያስታውሳል። ፊጦን በቀቢጸ ተስፋ ተውጦ የአባቱን የፊቦስን ምክርና ትዕዛዝ ጥሶ፥ የጸሓይ ሠረገላን ከመስመር አውጥቶ ባወረደው ምጣት ሰማይ በእሳት ጉም ሲሸፈን፥ ኢትዮጵያውያን በወላፈኑ ሲጠቁሩ፥ አባይም ተኖ ከማለቁ በፊት ራሱን ጋሬ ውስጥ ሲቀብር እናት ምድር ተንበርክካ ፈጣሪዋ እንዲማለዳት መለመኑዋን የግሪኮች ሚት እንደሚነግረን ሁሉ የንጉሥ ጊሎ እናት አካንጎም ከነበልባሉ ዘንዶ፥ ከኦቴኖ ፊት ቆማ የአገሪ አኙዋ ፍጻሜ ከመድረሱ አስቀድሞ ምህረት እንዲያወርድ ትማጠናለች። እሱም አማላጅነቷን ተቀብሎ ከዘንዶነት ወደ ቀድሞው ቅርጹ ይለወጣል። አካንጎም በቅል ውስጥ ከትታ ባሮ፥ ኦፔኖ፥ ወንዝ ላይ እንድትጥለው ይጠይቃታል። እሷም ያዘዛትን ስለፈጸመች ኦቴኖ በፈቃዱ ወደ ውሃ ይመለሳል።

ኦቴኖ ዛሬም አለ ተብሎ እንደሚታመንበት ሁሉ በተለይም በ 19ኛው ምዕት ዓመት መጨረሻ «ወደ ነጭነት ተቀይሮ መጣ» በሚል እምነት በአኙዋዎች ዘንድ ሽብርና ግርግር የማስከተሉ ድርጊት «ካርጐ ሙቨመንት» ወይም «ካርጐ ሚት» እየተባለ የሚጠቀሰውን ታሪካዊ ወቅት በዚህ አጋጣሚ እንድናነሳ ይጋብዛል፡፡ ድርጊቱም በታሪኩ መጨረሻ ላይ እንደሚከተለው ተገልጿል፡፡

> አንንጐም ትልቅ ቅል አምጥታ ኦቴኖን ከትታ ኦፔኖ፥ ባሮ፥ ወንዝ ላይ ጣለችው፡፡ ከዚህ በኋላ አገሩ ሰላም ሆኖ ኖረ፡፡ ግን . . . በኋላ 'በሱዳን ጠረፍ ኦቴኖ ወደ ነጭነት ተቀይሯል' ተብሎ ወሬ ተወራ፡፡ . . . በዚህ ጊዜ እንደገና አኙዋ በሽብር ተዋጠች፡፡ የጭሮ፥ የአዶንጐ፥ የአኮቦ፥ የጆር፥ ሌላው ቀርቶ የፑኝዶ አኙዋ ሁሉ ለቆ ወደ አቦቦና ወደ ደጋው በሽብር ተሰደደ፡፡ ኋላ ቆይቶ ሲረጋገጥ ግን. . . የእንግሊዝና የግብፅ ጦር መሆኑ ታወቀ፡፡ አገሩም እንደ ገና ሊረጋጋ ቻለ፡፡

ከትረካው መገንዘብ እንደሚቻለው በ1889 አመተምህረት ገደማ፥ የእንግሊዝና የግብፅ ሠራዊት ደቡብ ሱዳንን ይዞ በኢትዮጵያ ድንበር አካባቢ ሲታይ ለኦቴኖ ተሰጥቶት የቆየውን ባህርይ መሰረት በማድረግ በኦኙዋ ህብረተሰብ ዘንድ ተፈጥሮ የነበረውን ግርግር ለመረዳት የሜክሲኮው ልምድ እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል።

አዝቴኮች ዘወትር ጨለማን እየገፈፈ በብርሃን የሚተካ ጸሐይን ተሸክሞ የሚያዞር አንድ ኃያል አምላክ አለ ብለው ያምኑ ነበር። ይኸው የጸሐይ አምላክም ጸሐይን ተሸክሞ በመዞር ጨለማን ያህል ግዙፍ ኃይል በመግፈፍ ብርሃንን መተካት የሚያስችለው ጉልበት ይኖረው ዘንድ አገልጋዮቹ በየዕለቱ ደም እንዲቋደስና እንዲጠጣ የሰው መስዕዋት ያቀርቡለት ነበር። በተቃራኒውም ይህን የመሰለውን እምነትና በየእለቱ የሚቀርብ የሰው ግብር "ኮዛልኮትል" የተባለው ሌላው ኃያል አምላክ ክፉኛ ይቃወማል ተብሎ ይታመን ነበር። ስለዚህ "ኮዛልኮትል" አንድ ቀን ሳይታሰብ፥ በድንገት መጥቶ የጸሐይ አምላክንና አማኞቹን፥ አገልጋዮቹን፥ እንደሚደመስስ፥ ስርዓቱንም እንደሚሽር በአዝቴኮች ዘንድ እንደ ትንቢት አስቀድሞ ይነገር ነበር። በአዝቴኮቹ ምናብ ተቀርጾ ይኖር የነበረው ይኸው "ኮዛልኮትል" መልኩ ነጭ ሲሆን ጺሙም የተንዠረገገ ነው ተብሎ ይታመን ነበር። ይህ እምነት በህብረተሰቡ ስነልቡና ውስጥ ሰርፆ ሲኖር ከሜክሲኮ ምሥራቅ በሚገኘው በውቅያኖስ ዳርቻ ላይ ከዚህ በፊት ፍጹም ተሰምተውና ታይተው የማያውቁ ነጫጭና ጺማም ሰዎችን የያዙ ትልልቅ መርከቦች የመታየታቸው ወሬ እንደተዛመተ የ"ኮዛልኮትል" ፍካሬ ደረሰ ተብሎ በሜክሲኮ ከፍተኛ ድንጋጤና ግርግር እንደተፈጠረና በኋላም የድንጋጤው ምንጭ እንደተገመተው "ኮዛልኮትል" ሳይሆን የእስፓኝ ወራሪ ጦር መሆኑ ሲታወቅ ሞንቴዙማ የስፓኝን ጦር ህዝቡ በሰላም ተቀብሎ እንዲኖር አዘዘ። ግን ትንቢቱ አመፅን ቀስቅሶ የጸሐይ አምላክ አጣኝና ተገዥ የነበረው ሞንቴዙማ በደንጋይ ተወግሮ ሊሞት በቅቷል (McNeill 1979:396-397)። በኦኙዋዎች ዘንድም ይህን የመሰለው የቆየ እምነት በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ያስከተለው ፍርሃትና ግርግር ከአዝቴኮቹ ሽብር እምብዛም የተለየ ሆኖ አይገኝም።

ይኸውም፥ በ1517 ዓመተምህረት የጸሐይ አምላክ አገልጋይ በነበረው በሞንቴዙማ ዘመን ሜክሲኮ ውስጥ አዝቴኮች ለመጀሪያ ጊዜ ለወረራ የተሰማሩትን የስፓኝ ወታደሮች "ኮዛልኮትል" ስለተባለው ምናባዊ ፍጡር ይተረክ ከነበረው ሚትና ሲነገር ከቆየው ትንቢት ጋር በማያያዝ ከፈጠሩት ግርግር ጋር የኦቴኖ ሚትም ያስከተለው ሽብር ተመሳሳይ ሆኖ የመገኘቱ ክስተት ይሆናል።

ይህ ዓይነቱ ክስተትም አንድ ሕዝብ ለረዥም ዘመናት ይዞት ከቆየው የኮስሞሎጂ ወይም የስነፍጥረት ሀተታ፥ የእምነት ስርዓት፥ አመለካከትና ትርጓሜ ጋር በእጅጉ ቁርኝት እንዳለው Lawrence (1964) ይገልጻሉ። Lawrence እንደሚያስረዱት፥ በቀደምት አባቶቹ መናፍስት ወይም በተለያዩ አማልክት የሚያምን ሕዝብ "ካርጎ ሙቭመንት" ተብሎ በሚጠቀሰው ዘመን ለመጀመሪያ ጊዜ የስልጣኔ ውጤቶችን፥ ለምሳሌ፥ ሰማይ ሰንጥቆ እንደ መብረቅ እየተመመ የሚበርን አውሮፕላን ወይም ውቅያኖስ አቋርጦ የሚቀዝፍን መርከብ ለማየት ሲበቃ አብራሪዎቹ የአባቶቹ መናፍስት፥ አለዚያም አማልክቱ እንደሆኑ በማመን ለምን እስከዛሬ ተሰውረው እንደቆዩ በመደነቅ ደግመው "በበራሪ ቤት" ሲበሩና ሲቀዝፉ

ተአምራቱን በሲቃ ተሞልቶ ለማየት መጓጓት በታሪክ የተስተዋለ ክስተት መሆኑን ከኒው ጊኒ ልምድ በመነሳት ያስረዳሉ። የአኙዋው ኦቴኖም እንዲህ ያሉ በነባር ሚት፥ እምነትና ሎር (ዕውቀት) ላይ ተመስርተው ወይም ተዛምደው በአንድ የታሪክ ወቅት የተከሰቱ ሁኔታዎችና የተነገሩ ትረካዎች በሀገራችን ውስጥ ቢኖሩ ምን ባሕርያት፥ ቅርጽ፥ ተግባርና ውጤት እንደነበራቸው ወይም እንዳላቸው እንድንመረምር ይጋብዛል።

በአጠቃላይ ኦቴና መንፈሳዊና ሰብአዊ ፍጡር መሆኑን ከትንተናው እንገነዘባለን። Frye (1957) እንደገለጹት፥ ትረካው ሁለቱንም የሮማንስ ባህርያት ያካትታል፤ ወይም ደግሞ Okpecoho (1980) እንደሚያመለክቱት፥ "ሚቲክ-ሌጀንድ" ሊሰኝ ይችላል። ኦቴና Raglan ካቀረቧቸው የባህል ጀግኖችን ከሚያመሳስሏቸው መመዘኛዎች መካከል አብዛኞዎቹን ያሟላል:- የንጉሣውያን ቤተሰብ አባል ነው፤ የባለታሪኩ የአቀራረብ ስልትና የድርጊት ኃይሉም ከአንድ ስውር መንፈሳዊ ኃይል ጋር ቁርኝት አለው፤ ራሱን ብቻ ሳይሆን የሚመረምረው ህብረተሰቡንም ከሕልውናው፥ ከተፈጥሯዊ ግዴታው አኳያ ይፈታተነዋል። ስልጣን ላይ በመውጣትም ሰብአዊ ፍጡርነቱን ለማረጋገጥ ይጥራል። ተስፋ ግን ይርቀዋል። በዕጣው መዘውር እየተመላለሰ በሚገጥመው ውጣ ውረድም ለመጀመሪያ ጊዜ ለአኙዋዎች የኑሮ መሠረት ለሆነው የአደን ህይወትና ከጠላት ራሳቸውን ለመከላከል የሚያስችል የብረት ጦር፥ እንዲሁም ደስታና ሃዘናቸውን የሚገልጹባቸውን ቶምና ክራርን አበርክቶ ማለፉንም እንረዳለን።

በአኙዋዎች ዘንድ ልደትን አንድም በደስታ መቀበል፥ አለዚያም በድንጋጤ ተመልክቶ በሥውር ማስወገድ የተለመደ አሰራር ነው። ኦቴኖንም የሚገጥመው ፈተና አኙዋዎች ስለ ራሳቸውና ስለ ፈጣሪያቸው ባላቸው አመለካከት ከእሱ ጋርም ስላላቸው ግንኙነት ከሚሰጡት ትርጉም በመነሳት ከሚከተሉት ልማዳዊ አሰራር ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። በመሆኑም ግጭቱም ሆነ ታሪኩ በግል ሕይወትና በህብረተሰብ ሕልውና ዙሪያ ያጠነጥናል። በአንድ በኩል ኦቴና እውነተኛ የሰው ልጅ መሆኑን የሚኖርበት ህብረተሰብ እንዲያውቅለት ይታገላል። በሌላ በኩል ደግሞ ህብረተሰቡ የደህንነት ዋስትናውን ለማረጋገጥ ሲል ኦቴኖን ለማስወገድ ይፈልጋል። ይህ ግጭት በእምነትና በህልውና ጥያቄ መካከል የሚካሄድ ፍልሚያ ብቻ አይደለም። የሰው ልጅ የህይወት እንቆቅልሽና የእውኑ ዓለም ድርጊትና አስተሳሰብ በምናባዊ የፈጠራ ኃይል ገሃድ ሆኖ የቀረበበት የጥበብ ስልት ጭምርም የትረካው ቁም ነገርም በዚሁ መሰረታዊ ጉዳይ ላይ ያተኮረ ሆኖ ነው የምናገኘው። በመሆኑም ኦቴና በዘመን ርቀት ብቻ የሚታይ አይደለም፤ የዛሬውንና የነገውንም ጨምረን እንድናስብ የሚረዳ የለውጥ ጀግና እንጂ።

References

Bayleyegn Tasẹw. 2000. "Rivers of Wisdom: The Myth as Tenet of Justice in Aňyuaa." A Paper presented to the 14th International Conference of Ethiopian Studies, Nov.6-11, Addis Ababa University.

Birds, Charles S. and Martha B. Kendall. 1980. " The Hero: Text and Context." in *Explorations in African Systems of Thought* (Ivan Karp and Charles S. Birds eds.). Washington: Smithsoman Institute Press.

Campbell, Joseph. 1960. *The Hero with a Thousand Faces*. New York: Bollingen Foundation, Inc.

Frye, Northrop. 1957. *Anatomy of Criticism*: *Four Essays*. Princeton, New Jersey:, Princeton University Press.

Jung C.G. and C. Kerenyi. 1963. *Essays on a Science of Mythology*: *the Myth of the Divine Child and the Divine Maiden.* New York and Evanston: Harper and Row, Publishers, Inc.

Kunene, Mazisi. 1980. " The Relevance of African Cosmological System to African Literature Today." In *African Literature Today 11: Myth and History* (Eldred Durosimi Jones ed.) New York: African Publishing Company, pp.190- 205.

Lawrence, Peter. 1964. *Raod Belong Cargo*: *A Study of the Cargo Movement in the Southern Madang District of New Guinea*. Oxford: Manchester University Press.

McNeill, William H. 1971. *The Ecumene*: *Story of Humanity*. New York: Harper and Row, Publishers.

Muana, Patrick Kagbeni . June 1998. " Beyond the Frontiers: a Review of Analytical Paradigm in Folklore Studies." In *Journal of African Cultural Studies*. Vol.11, No.1, pp.38-58.

Okpewho, Isidore. 1980. "Rithinking Myth." In *African Literature Today 11: Myth and History*. (Eldred durosimi Jones ed.), New York: African Publishing Company, pp. 5-23.

- - - - - . 1975. *The Epic in Africa*: Towards a Poetics of the Oral Performance. New York: Columbia University Press.

Pascal, Boyer. 1990. *Tradition as Truth and Communication: A Cognitive Description of Traditional Discourse*. Cambridge: Cambridge University Press.

Perner, Conradin. 1991. *A Short Grammar and Dictionary Preceeded by an Essay on the Role of Language in Anyuak Society* (Vol. 1). New Haven, Connecticut: Human Relations Area File, Inc.

Raglan, Lord. 1965. "The Hero of Tradition." In *The Study of Folklore*. (Alan Dundes, ed.) Eglewood Cliffs, N.J.: Printice Hall, Inc.

Stauder, Jack. 1971. *The Majangir: Ecology and Society of a Southwest Ethiopian People*. Cambridge: Cambridge University Press.

ፈቃደ አዘዘ፣ ሰኔ 1970፣ "የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አፋዊ ቃል ጥናት፣ የቋንቋ ጉዳይ በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወቅት"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለተካሔደ ሴሚናር የቀረበ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

7. አባሪ

ኦቴና*

ጥንት ኦቴናና ጊሎ የሚባሉ የእህትማማች ልጆች ነበሩ:: የኦቴና እናት ኚች ትባላለች:: የጊሎ እናት ደግሞ አካንጎ ትባል ነበር:: የጊሎ አባት ኚያ፣ ንጉሥ ነበር:: ኦቴናና ጊሎ የተወለዱት በአንድ ቀን ሲሆን አፈጣጠራቸው ግን እጅግ በጣም የተለየ ነበር:: ኦቴና እጅግ በጣም አጭር፣ ድንክ ነበር:: ድንክ ከመሆኑ በላይ ሲወለድ ግርዝ ሆኖ ነበር:: ሲያዩትም የሚያስጠላ አስቀያሚ ፍጡር ነበር:: ጊሎ ግን ደስ የሚልና እጅግ በጣም የሚያምር ረጅም ለግላጋ ልጅ ሆኖ ተወለደ:: ኦቴና ድንክ፣ ግርዝና ለዓይን የሚያስጠላ ሆኖ በመፈጠሩ ምክንያት ሁሉም ሰው፣ ዘመዶቹ፣ እናቱና አባቱ እንኳን ሳይቀሩ ጠሉት:: እናቱ ኚች እና አባቱ "ምን ብንሆን ነው እንዲህ ያለ ልጅ የወለድነው?" እያሉ በጣም ያዝኑ፣ ይጨነቁ፣ ይስቀቁና ያፍሩ ነበር:: ሆኖም ኦቴናን ከወለዱ በኋላ ብዙ አልቆዩም:: ሁለቱም በሀዘንና በስቀቀን በተከታታይ ሞቱ:: እናት አባቱ ከሞቱ በኋላ ኦቴና ከአባቱ ቤት እንዲኖር ተደረገ:: ግን ኦቴናን ሁሉም ሰው ስለጠላው እሱ የጠጣበትን ዕቃ ሌላ ሰው አይጠጣበትም ነበር:: እሱ የበላበትን ዕቃ ማንም ሰው አይነካውም ነበር:: ኦቴና የነካው እህል እሩቅ ቦታ ይደፋ ነበር:: ፀሐይ እንዲመታው የተሰጣ ክክ፣ ዱቄት ወይም የአሳ ቋንጣ ኦቴና ተራምዶት ካለፈ ውሃ ውስጥ ይጣል ነበር:: ከእሱ ጋር ሰው አብሮት እንዲያድር ወይም እንዲተኛ አይፈቀድለትም ነበር:: ኦቴናን የሚነካውና የሚቀርበው አንድ ሰው አልነበረም:: ሴቶች ገና ከሩቅ ሲያዩት "ች-ጀክ"፣ "ች-ጀክ"፣ ቡዳ፣ እያሉ የያዙትን ዕቃ እየጣሉ በድንጋጤና በፍርሃት በርግገው ይሸሹ ነበር:: ከአባቱ ቤት ሆኖ እንዲኖር ሲደረግ የአባቱ ሚስቶች ወይም የእንጀራ እናቶቹ በጣም ስለተጠየፉትና ስለፈሩት ሲያዩት ሩጠው ወደ ቤታቸው በመግባት ይደበቁታል:: ወደ ቤት ገብቶ ሲመጣባቸውም ይጮኹበትና ውጣ፣ ውጣ፣ ውጣ፣ ፖዳኖ ሰው ያልሆነ እርኩስ እያሉ ያበርሩታል:: የሚበላውን ምግብና የሚጠጣውን ውሃ ያመጡበት ዕቃም እንዳይነካካ በማድረግ ሳያያቸው ገልብጠው አስቀምጠውለት ይመለሱ ነበር:: አክስቱ አካንጎም እንደ አባቶቹ ሚስቶች ወይም እንደ እንጀራ ኦናቶቹ የሚበላውንና የሚጠጣውን አስቀምጣ ትሄዳለች እንጂ ምግብና ውሃ ያመጣችበት ዕቃ እንኳን እንዲነካካ አታደርግም ነበር:: ኦቴና ሰው ሁሉ እንደዚህ ጠልቶት ብቻውን ሲኖር ከቤተሰቡ መካከል እጅግ በጣም ይወደው የነበር የንጉሡ ልጅ ጊሎ ብቻ ነበር::

ጊሎ የእናቱ የእህት ልጅ ነው:: ጊሎ ኦቴናን እንዳይቀርበው፣ እንዳይነካው አብሮትም እንዳይሄድ ዘወትር ቢነገረውም እሽ ብሎ አይቀበልም ነበር፤ አይሰማም ነበር:: ኦቴናም ከጊሎ ሌላ ማንም ስለማይቀርበው ከጊሎ መለየትን ፈጽሞ አይፈልግም ነበር:: እና ጊሎ ለጨዋታ ወደ ወንዝ ሲሄድ እሱም ተከትሎት ይሄዳል::

---

*(ይህን የተረኩት አቶ አበላ ኛግዎ የተባሉ በጋምቤላ ከተማ የሚኖሩ የስማኒያ ሰባት ዐመት አዛውንት ናቸው የካቲት 11 ቀን 1990 ዓ.ም. ከሰዓት በፊት::)

እሱ ወደ ጊሎ ሲጠጋ ግን ከጊሎ ጋር ይጫወቱ የነበሩ ልጆች ሁሉ ሰይጣን የመጣባቸው ይመስል "ች-ጆክ"፣ ፓዳኖ፣ እያሉ ዞረው ሳያዩ በርግገው ይሮጣሉ:: በተለይም ልጃገረዶች እጅግ በጣም በጣም ይፈሩት ስለነበር ተኩላ እንዳየ ፍየል ይሸበሩና ይሸሻሉ:: ገና ሲመጣ "ኦቴኖ ሰው ያልሆነው ፍጡር! ኦቴኖ ፓዳኖ ኦቴኖ ግርዝ ቁላ! ኦቴኖ ቾ-ጆክ" ኦቴኖ የጆክ ሚስት! እያሉ እየተጯጯሁ ዞረው ሳያዩ ይበረግጋሉ:: ውሃ የሚሄዱ ሴቶችም እንደዚያው እየተንጫጩ ዕቃቸውን ጥለው ይበረግጉ ነበር::

ልጃገረዶችና ሴቶች ኦቴኖን እንዲህ ሲፈሩትና በጣም ሲጠሉት ጊሎን ግን እስቲያገኙት፣ እስቲያዩት፣ በጣም ይቸኩሉና ይጣደፉ ነበር:: ልጃገረዶች ጊሎን በጣም ይወዱት ነበር:: ጊሎ ቁመቱ ረጅም፣ ወፍራም፣ ዓይኑ ዛጎል የሚመስል ነበር:: ቁመቱ፣ መልኩ የሚያምር ስለነበር ልጃገረዶች ጊሎን ሲያዩ ይከቡታል:: ከጊሎ ተለይተው መሄድ ሞት መስሎ ይታያቸዋል:: ጊሎን በመልኩና በቁመናው ማማር ሴቶች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ይወደው ነበር:: ግን መልክና ቁመናው ያማረ፣ የተዋበ ቢሆንም ጊሎ እንደ ኦቴኖ ብልህና አዋቂ አልነበረም:: ክፉን ከደግ ለይቶ አያውቅም:: አርቆ አያይም ነበር:: ይህ ቢሆን ክፉ ነገር ያመጣል፣ ክፉ ነገር ይገጥመኛል ብሎ አይጠረጥርም:: አዙሮ አያይም፣ ጊሎ ገር፣ ሞኝ፣ ደግና አዛኝ ሰው ነበር:: እናቱ አካንጎ ከኦቴኖ ጋር እንዲገናኝ ፈጽሞ አትፈልግም ነበር:: እሱን ሲያይ እንደሌላው ሰው እንዲሸሽ፣ እንዲርቅ፣ አዘውትራ ትነግረውና ትመክረው ነበር:: ጊሎ ግን "ከኦቴኖ ጋር አትገናኝ" ሲሉት በጣም ይከፋል:: እንዲያውም ኦቴኖን ካላገኘ ፈጽሞ ደስተኛ አይሆንም ነበር:: ኦቴኖም ጊሎን ከመጠን በላይ ይወደው ስለነበር ከእሱ መለየት በፍጹም አይፈልግም ነበር:: ሁለቱ በአፈጣጠራቸው እንደሚለያዩ ሁሉ በብስለትም የተለያዩ ነበሩ:: ጊሎ ብስል አልነበረም:: ኦቴኖ ግን ማንም የሚደርስበት ሰው አልነበረም:: ሰው የሚያስበውን በማየት ያውቃል:: ብልህ፣ ብልጥ፣ ዘዴኛና አዋቂ፣ ተንኮለኛ ነበር:: ከሕፃንነት ዕድሜው አንስቶ ድርጊቱ፣ ሥራውና አነጋገሩ ሁሉንም የሚያስገርም፣ የሚያስደንቅ፣ የሚያስደነግጥ ፍጥረት ነበር:: ከዚህ በላይ ፍርሃት አልነበረውም:: ደፋር፣ ሩጦ የማይያዝ፣ ፈጣን ስለነበር ሥራውና ድርጊቱ ከሰው የተለየ ነበር:: አጭር፣ ድንክ፣ አቅመ ቢስ ቢመስልም ጉልበቱን፣ ቁጣውንና የሚያደርሰውን ጉዳት ማንም ሰው አይቋቋመውም ነበር::

ኦቴኖ ዕድሜው እየጨመረ በሄደ ቁጥር "ሰው ሁሉ ለምን ይጠላኛል? ለምን "ች-ጆክ"፣ ፓ-ዳኖ"፣ "ግርዝ" ይለኛል? በተለይም ልጃገረዶችና ሴቶች እኔን እየሸሹ ጊሎን ለምን ይወዱታል!" እያለ ያስብና ያብሰለስል ነበር:: ይህን ጥያቄ ሁል ጊዜ ጊሎንና አክስቱን አካንጎን ይጠይቃቸው ነበር:: እነሱ ግን ዝም ይሉታል እንጂ መልስ አይሰጡትም:: በዚህም ይናደድ ነበር:: ኦቴኖ በዕድሜ እየበሰለ፣ እያደገ በሄደ ቁጥርም ከአባቶቹ ሚስቶች፣ ከወንድሞቹና ከእህቶቹ፣ ከዘመዶቹ ጋር ማታ ማታ ሰው ሁሉ በእሳት ዙሪያ ተሰብስቦ ራት ከሚበላበትና ከሚያመሽበት ከዊማች አብሮ ለመብላት፣ ለመጫወት፣ ለመዝናናት ሲፈልግ የመንደሩ ሰው ሁሉ ሂድ ጥፋ ጥፋ በማለት ከዚያው ከአባቱ ቤት ብቻውን እንዲቀመጥ ያስገድደው ነበር:: እሱ ግን እንቢ በማለት ወደ ዊማች ገፍቶ ከመጣ ሁሉም ይሸሽና ወደየቤቱ ገብቶ ቤቱን ዘግቶ ቁጭ ይላል:: በዚህም በጣም ያዝን፣ ይተክዝ፣ ያለቅስ ነበር:: ምንም እንኳን አባቱና

እናቱ በሕፃንነቱ ቢሞቱም የአባቱ ሚስቶች የእሱ ሚስቶች ናቸው:: ሆኖም "ከእኔ ጋር ተኙ" ሲላቸው "እምቢ" ይሉታል:: በዚህም ኦቴና በጣም ይናደድ ነበር:: አንድ ቀን አንዷቱን የእንጀራ እናቱን አብራው እንድትተኛ ነገራት:: እሷ ግን "እንኳን አብሬህ ልተኛ ዓይንህን ለማየት እፈራለሁ፣ ብሞት አልመጣም" አለችና መለሰችለት:: እሱም "ካልመጣሽ እገድልሻለሁ" አላት:: በመጨረሻም ከሩቅ አገር ልትጠይቃት የመጣች እህቷን "ሂጂና ምን እንደሚፈልግ ጠይቂው እስቲ" አለቻት:: ሞኚቱ ሴትም ኦቴና "ኑ" እያለ ከሚጠራበት ቤት ድረስ ሄደችና "ምን ፈልገህ ነው ትልሀለች" አለችው:: እሱም ተናደደና "አባቴ ያወረሰኝን ሚስቶቼን አልኩ እንጂ አንችን ማን ጠራሽ?" አላት:: ሴትዮዋም "የመጣሁ እህቴ 'ምን ፈልጎ ነው? ጠይቂው' ስላለችኝ ነው . . . " ብላ ዞር ስትል ኦቴና እንደወፍ ብርርር ብሎ መጣና መሀል ራሷን በቆመጥ መታት:: ሴቲቱም ድምጽ ሳታሰማ በአንድ ጊዜ ፀጥ አለች፣ ሞተች:: ከዚያም ኦቴና መሞቷን እንዳረጋገጠ በቆርበት ጠቀለለና ከቤቱ ውስጥ አስቀመጣት::

ከዚያ በኋላ እህቷ "ለምን በዚያው ቀረች?" እያለች ስታስብ ሌሊቱ ነጋ:: ከነጋ በኋላም ልትመጣ አልቻለችም:: በመጨረሻ እህቷ ተስፋ ቆረጠችና ለመንደሩ ሴቶችና ለአባቱ ሚስቶች "እህቴን ከኦቴና ቤት ማታ ልኬያት ነበር:: በዚያው ቀረችብኝ" ብላ ነገረቻቸው:: ሰው ሁሉ ይህን እንደሰማ በድንጋጤ "ምን ልታደርግ ከኦቴና ቤት ገባች? ቂል ነበረች እንዴ?" ብሎ አሾፈባት:: ኋላም የሄደችበትን ሁኔታ ዘርዝራ አንድ በአንድ ነገረቻቸው:: በመጨረሻ ኦቴና ከቤቱ ወጥቶ የሄደ መሆኑን በማረጋገጥ ወደ ቤቱ ሰው ሁሉ ገባና ሴትዮዋን ሲፈልግ ሞታ በቆዳ ተጠቅልላ ወድቃ አገኛት:: ሰው ሁሉ በአሟሟቷ እየተገረመ ኦቴና ገና ሁላችንን ይፈጀናል" እያለ ሲጨነቅ የጊሎ አባት፣ ንጉሡ ሞተ::

ንጉሡ እንደሞተም በምትኩ ንጉሥ ይመረጥ ተባለ:: ከዚያም የአገሩ ሰው እየተሰበሰበ ማን ከማን ይሻላል እያለ ከመከረና ከተስማማ በኋላ ጊሎን መርጦ በሮኒ (በሥርዐተ ንግሥ) ኚያ፣ ንጉሥ፣ አደረገው:: አገሩ እየተሰበሰበ ሲመክር፣ ሥርዓተ ንግሥ ሲፈፀም ግን ኦቴና አያውቅም ነበር:: በመሆኑም ጊሎ ኚያ ሆኖ መመረጡንና መንገሡን በሰማ ጊዜ በጣም ተናደደ:: "የአገሩ ሰው በሙሉ እኔ ምርጫውንና የንጉሡን ሥርዓት እንዳላይ ለምን ይደብቀኛል? እኔ ሰው አይደለሁምን?

እኔስ የንጉሥ ዘር አይደለሁምን? ልመረጥ አልችልንም? ጊሎ ከእኔ ምን የተሻለ ዕውቀት አለው? እኔ አልሻለውም ነበር ለአገሩ?" አለ:: ቀድሞም ኦቴና ጊሎን ቢወደውም ይቀናበት ነበር:: ልጃገረዶች፣ ሴቶች ሁሉ "ጊሎ፣ ጊሎ" እያሉ በዙሪያው ሲከቡ፣ ሲያሽካኩ እሱን ግን "ቾ ጆክ"፣ "ፓ-ዳኖ"፣ "ድንክ"፣ ግርዝ እያሉ ለማየት ሲጠየፉትና ሲበረግጉ፥ አሁን ደግሞ ጊሎ ንጉሥ ሲሆን የአገሩ ሰው ሁሉ ጠላት ሆኖ ታየው:: በመጨረሻም እጅግ በጣም ይወደው የነበረውን "ጊሎን መግደል አለብኝ" አለና በልቡ ወሰነ:: "ጊሎን ብገድለው እሱን ለማግኘትና ለመንከባከብ የሚፈልጉትን፣ የሚያፈቅሩትና የሚወዱትን ሴቶች ሁሉ ልባቸውን አሳርረዋለሁ" አለ:: ኋላም ዘዴ በመፍጠር ኦቴና ንጉሥ ጊሎን "ወደ አደን እንሂድ፣ ለብዙ ጊዜ ሥጋ አልበላንም:: ሥጋ ያስፈልገናል፣ አደን ብንሄድ ምን ይመስልሃል" ብሎ አማከረው:: ንጉሥ

ጊሎም በኦቴኖ ሀሳብ ተስማማ። ኦቴኖም ጊሎ በሀሳቡ መስማማቱን እንዳወቀ" ሌላ ሰው አብሮን መሄድና የምንሄድበትን አቅጣጫ ማወቅ አይኖርበትም። አደራህን ጊሎ ከእኔ ጋር ለአደን መሄድህን ማንም ሰው ማወቅ የለበትም። ለአደን ልንሄድ ነው ካልክ ሰው ይከተልሃል። ስለዚህ ሰው ሳያይ ብቻህን ውጣ" አለው። ንጉሥ ጊሎም "እሺ! ሰው ሳያይ በሌሊት እንሄዳለን" በማለት ተስማማ። ከዚህ በኋላ ኦቴኖ "ከዕኩለ ሌሊት በኋላ ሰው ሁሉ ሲተኛ ውጣ" አለውና የሚገናኙበትን ቦታ ወሰኑ። ቦታው ከሚኖሩበት አገር በጣም የራቀ ነበር። ለመገናኘት የተነጋገሩበት ቦታም ሁለቱ ከዚህ በፊት ከሚያውቁት ከአንድ ከትልቅ ዋርካ ስር ነበር። በመጨረሻም ኦቴኖና ንጉሥ ጊሎ "ቀድሞ የደረሰ ከዋርካው ስር ይቀመጥና ይጠብቅ" ተባብለው ተቀጣጥረው ተለያዩ። በዚያ ዘመን እንደ ዛሬው ከብረት የተሰራ ጦር አልነበረም። ጊሎም ኦቴኖም የያዙት ከዝሆን ጥርስና ከአጥንት የተሰራ ጦር ነበር።

ተቀጣጥረው እንደተለያዩ ኦቴኖ አቴሮ፥ ቁላ ጦር፥ ይዞ ወደ ተቀጣጠሩበት ቦታ ከእኩለ ሌሊት በፊት ሄደ። ጊሎም እንደዚሁም ሙርቶንግ፣ እምስ ጦር፣ ይዞ ከእኩለ ሌሊት በኋላ ሰው ሁሉ ሲተኛ ከቤተ መንግስት ሳይታይ ሾልኮ ውሻውን አስከትሎ ሄደ። ከተቀጣጠሩበት ቦታ ቀድሞ የደረሰው ኦቴኖ ነበር። እንደደረሰ ከዋርካው ላይ ተሰቀለና ንጉሥ ጊሎ እስኪመጣ ድረስ መጠበቁን ቀጠለ። ጊሎ ግን ከእኩለ ሌሊት በፊት ሰው ሁሉ ከዊማች ተነስቶ ከቤቱ እስኪተኛ ድረስ ከቡራው ወጥቶ ሳይታይ ለመሄድ አይችልም ነበር። ስለዚህ ሰው ሁሉ ጦሩን ይዞ ውሻውን አስከትሎ ማንም ሳያየው ጀቡራዎቹ፣ ዘቦቹ፣ ሁሉ አፍላ እንቅልፍ ይዟቸው ሳይነቁ ኦቴኖ ወደ ቀጠረው ቦታ ሄደ። ሌሊቱን ተጉዞ ለመገናኘት ከተቀጣጠሩበት ቦታ እንደደረሰ ኦቴኖ ቀድሞ መጥቶ እንደሆነ በማለት የዋርካውን ዙሪያ ቃኘ፣ አየ። ከዚያም ተኝቶ ሊሆን ይችላል በሚል "ኦቴኖ! ኦቴኖ! ኦቴኖ!" ብሎ ደጋግሞ ቢጣራ፥ አሁንም ደጋግሞ ቢጣራ ቢጣራ፥ ኦቴኖ መልስ ሊሰጠው አልቻለም። እንደ አሸኮኮ ከዋርካው ጫፍ ወጥቶ ቁጭ አለና ጊሎ ብቻውን መምጣቱን፣ ከዚያም የሚያደርገውን፣ የሚሰራውን ሁሉ አቆልቁሎ በማየት ድምፁን አጥፍቶ ዝም አለ። ከዚያም ንጉሥ ጊሎ "ባይመጣ ነው እንጂ፣ ቢመጣ ለመገናኘት የተቀጣጠርነው ከዚህ ከዋርካው ስር አልነበር። ገና ባይመጣ ነው፣ ፈቅ ብሎ ቢተኛ ደግሞ ስጠራው ይሰማኝ ነበር። ውሻውም በጠረኑ አሽትቶ ምልክት ሊሰጠኝ ይችል ነበር። ባይመጣ ነው እንጂ" አለና ኦቴኖ እስኪመጣ ድረስ ለመጠበቅ "ከዋርካው ሥር ቁጭ ብየ ልጠብቅ" አለ። ውሻውም አልጮኸም ወይም ምልክት አልሰጠም። ዋርካው ትልቅና ረጅም ስለነበር ጠረን አልሸተተውም። ስለዚህ ውሻውም ከንጉስ ጊሎ ጎን ቁጭ አለ። ደኑና ዱሩ ፀጥ ብሏል፤ አንድም ኮሽታ አይሰማም። በዚህ ጊዜ ኦቴኖ ከዋርካው ጫፍ ቅርንጫፉንና ቅርንጫፉን ተደግፎ ተደላድሎ ቁጭ እንዳለ ንጉሥ ጊሎን ከተቀመጠበት አቆልቁሎ አየው። ከዚያም ቀስ ብሎ አነጣጥሮ በጊሎ አናት ትይዩ ደጋኑን ሳበና ጦሩን ለቀቀው። ያ ጦርም ከጊሎ መሀል አናት ላይ ተሰካ። ንጉሥ ጊሎም በኃይል ጮኸ። ከዚያም ከዋርካው ሥር ተዘርግቶ ወደቀ። በዚህ ጊዜ ውሻው ወዲያ ወዲህ እየሮጠ፣ የዋርካውን ዛፍም እየዞረ ጮኸ። አለቀሰ። የጊሎን መሞት እንዳየ ከፈሰሰው ደም ላይ ተንከባለለ። አፉንና አገጩን ሁሉ በደሙ ተቀብቶ እያለቀሰ ወደ ሰፈሩ እንደ እብድ እየሮጠ እየከነፈ ሄደ። ከሰፈሩ እንደደረሰ ሰው ሁሉ ከእንቅልፉ ተነስቶ ነበር። ጉህ ቀዶ ወፍ ይንጫጫ ነበር። ከቡራው፥ ማለትም፥ ከንጉሡ ሠፈር እንደደረሰ በወለሉ እየሮጠና እየተዘዋወረ "እ !እ! እ!"

እያለ ጅራቱን እያወዛወዘ በሚያሳዝን ሁኔታ እያለቀሰ መጮኹን ቀጠለ፡፡ በዚህ ጊዜ ሰው ሁሉ "ይህ ውሻ ምን ሆኗል? የተቀባው ደምስ የምን ደም ነው? ካለወትሮው እንዴት እንደዚህ ያለቅሳል?" እያለ በድንጋጤ ማየት ጀመረ፡፡ የንጉሥ ጊሎ እናት አካንጎም ወደ መኝታ ቤቱ ገባች፡፡ ከዚያም "ጊሎ! ጊሎ! ጊሎ! አንተ ልጄ ጊሎ" እያለች ደጋግማ ጠራችው፡፡ አካንጎ ልጇን ብትጠራው፣ ብትጠራው ፈጽሞ መልስ አላገኝ አለች፡፡ ወዲያውም "ምን ሆኗል ልጄ ዛሬ" በማለት ደንግጣ ወደ መኝታ ቤቱ ገባች፡፡ ንጉሥ ጊሎ ከመኝታ ቤቱ ውስጥ የለም፡፡ በዚህ ጊዜ እናቱ አካንጎ በጣም ደነገጠችና "ልጄ ጊሎ የት ሄዷል?" ብላ ጮኸች፡፡ ከመኝታ ቤቱ ወጥታም ጀቡራዎችን፣ ዘቦችን፣ ከነጋ አይተውት እንደሆነ ለማወቅ ጠየቀቻቸው፡፡ እነሱም ከነጋ አላየነውም፡፡ ግን ከቡራው፣ ከቤተመንግሥቱ፣ ውጭ አልሄደም አሏት፡፡

በኋላ ከቡራው ውስጥ የሚገኙት ቤቶች ሁሉ ቢፈተሹ ንጉሥ ጊሎ ሊገኝ አልቻለም፡፡ ሁለም ሰው ግራ ገብቶት ሲጨነቅ ውሻው አሁንም እንደዚያው በሚያሳዝን ሁኔታ ያለቅስ ነበር፡፡ አካንጎ እና ሰው ሁሉ በመደንገጥ ቡል (ነጋሪት) እንዲመታ ተደረገ፡፡ ቡሉ ተመትቶ እንዳስገመገመ ያገሩ ሰው ሁሉ ከየአቅጣጫው በድንጋጤ እየሮጠ በመምጣት በቡራው ዙሪያ ተሰበሰበ፡፡ ሴቱ፣ ወንዱ፣ ትንሹ፣ ትልቁ፣ ከየአቅጫጫው መጣና "ምን አስደንጋጭ ነገር ተፈጠረ? አገራችን ሰላም አይደለምን? ጠላት መጣን? ቡል የተመታበት ምክንያት ምንድን ነው? እንስማና እንወቅ" አለ፡፡

አካንጎም "ንጉሥ ጊሎ ጠፋብን፣ እስከምንተኛ እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ አብሮን ነበር፡፡ አሁን የት እንደገባ ጠፋብን" ብላ ለሕዝቡ ተናገረች፡፡ ቡል ሲመታ የአገሩ ሰው እንደተሰበሰበው ሁሉ ጊሎም በህይወትና በጤናው በቅርብ ቦታ ቢኖር ወደ ቡራው ይመጣ ነበር፡፡ አልመጣም፡፡ ስለዚህ ሁሉም በደህናው አልጠፋም" አለና በጭንቀት ተዋጠ፡፡ የውሻውንም ሁኔታ በማየት ተጨነቀ፡፡ ኋላም በየአቅጣጫው ለፍለጋ ለመሰማራት ሲነሳ ኦቴኖ መጣ፡፡ ወዲያውም እንዲህ በማለት ተናገረ፡፡ "ጊሎ ወዴት እንደሄደ አልታወቀም፡፡ በርግጥ መፈለግ አለብን፡፡ ከመፈለጋችን በፊት ግን አገሩ ንጉሥ ሊመርጥ ወይም ሊኖረው ይገባል፡፡ ዙፋኑ ባዶ ሊሆን አይገባም፡፡ ስለዚህ ከአሁኑ ሰዓት ጀምሮ እኔ የአገሩ ንጉሥ ሆኛለሁ፡፡ ጊሎን ከእኔ የበለጠ የሚወደው ማንም የለም፡፡ እናንተ ብትተዉት እኔ እፈልገዋለሁ፡፡ ነገር ግን ተፈልጎ እስኪገኝ ዙፋኑ፥ ቡራው፣ ንጉሥ ያስፈልገዋል፣ ንጉሡም እኔ ነኝ፡፡ ጊሎ ያክስቴ የአካንጎ ልጅ በመሆኑ ከዚያም በላይ ስለምወደው ሚስቶቹ፣ ሀብቱ፣ ንብረቱ ሁሉ የእኔ መሆኑን እወቁ!" በማለት ለህዝቡ ተናገረ፡፡

ሕዝቡም ይበልጥ በመደናገጥ "አንተ ንጉሥ ልትሆን አትችልም፡፡ ቺ-ጆክ ነህ፡፡ ምክንያቱም ስትወለድ ግርዝና ድንክ ሆነህ ነው፡፡ አንተ እንዴት የአገሩ ንጉሥ ልትሆን ትመኛለህ፡፡ እኛስ እንዴት ንጉሥ ሁኑን ብለን ልንመርጥህ እንችላለን፡፡ የማይሆን አይሆንም፡፡ ጊሎም በህይወት መኖሩ አያጠራጥርም፡፡ ምኞትህ ከንቱ ነው" በማለት ሰው ሁሉ ተቃወመ፡፡ በዚህ ጊዜ ኦቴኖ "ወደዳችሁም ጠላችሁም ጊሎን ፈልጌ እስከማገኝ እኔ የእናንተ ንጉሥ ነኝ" አለ፡፡

ከዚህ በኋላ ህዝቡ ኦቴኖን ቀጥቅጦ ለመግደል ተነሳ። ጦርነቱ ተጀመረ። ኦቴኖ በአንድ በኩል ሆኖ ህዝቡን ብቻውን ገጠመው። ብዙ ህዝብ አለቀ። ኦቴኖ ዘዴው፣ ጥበቡ፣ ጉልበቱና ፍጥነቱ የሚቻል አልነበረም። በመጨረሻም ህዝቡ ተበታተነ። ኦቴኖ ድል ተቀዳጀ። ከዙፋኑ ላይ እንደተናገረው ተቀመጠ። የጊሎን ሀብትና ሚስቶች ሁሉ ወረሰ። ከቡራው ገብቶ ተቀመጠ። አገሩንም መግዛት ቀጠለ። ህዝቡ ግን ውስጥ ወስጡን አጌም፣ አመፅ፣ ማካሄዱን ቀጠለ። ያገሩ ሕዝብ "ፓ-ዳኖ" ሰው ያልሆነ ግን ሰው የሚመስል ፍጡር፣ በዙፋን ላይ ተቀመጠ። በቃ እንግዲህ የጥፋት ዘመን መጣ" በሚል አጌም፣ አመፅ፣ ጀመረ። ኦቴኖን ለመግደልም የመጨረሻ ውጊያ ለማካሄድ በመሞከር ላይ እንዳለ የንጉሥ ጊሎ እናት አካንጎ የውሻውን ደም ተቀብቶ መምጣትና አሳዛኝ ሁኔታ ከኦቴኖ ንጉሥ ነኝ ባይነት ጋር የልጇን ሳይታሰብ ጠፍቶ መቅረት በማቆራኘት በአእምሮዋ ማሰላሰል ጀመረች። በኋላም "ጊሎን የገደለው ኦቴኖ መሆን አለበት" በማለት አመነች። ይህን እምነቷንም ያገሩ ሰው እንዲረዳው አደረገች። ሕዝቡም የአካንጎን ቃል በመቀበል "ዕውነት ነው፣ ኦቴኖ ንጉሥ ጊሎን ገድሎታል። ሲገድለውም ውሻው አይቷል። የተቀባው ደምም የንጉሥ ጊሎ ደም መሆን አለበት" ብሎ አመነ። ከዚያም ሕዝቡ ውሻውን ይዞ ለፍለጋ በየጫካው ተሰማራ። በመጨረሻም ንጉሥ ጊሎ ከራሱ ላይ በጦር ተወግቶ ሞቶ ከወደቀበት ከዋርካው ሥር በውሻው መሪነት ተገኘ። ከዚያም በኋላ አካንጎ "ልጄን ጊሎን ምን አጥፍቶ ገደልከው? በዕውነት ትወደው አልነበረምን? እሱስ ይወድህ የነበረ ብቸኛ ወንድምህ አልነበረምን? ብላ እያዘነች ወቀሰችው። ቀጥላም "ስለገደልከው ወደ ውሃ ተይዘህ መጣል ይገባሃል" አለችው።

እሱም "አካንጎ የጊሎ እናት የእኔ እናት ነሽ፤ አክስቴ እናቴ ነሽ፤ ጊሎን እንደምወደው እሱም እንደሚወደኝ ታውቂያለሽ። ታዲያ ብገድለው መጥረቢያ ከእነእጀታው ወደ ውሃ መወርመር ለምን ፈለግሽ?" እያለ መለሰላት።

ኦቴኖ ንጉሥ ጊሎን ከገደለበት ቀን አንስቶ ልቡ በሃዘን ተወግቶ ነበር። "ጊሎን ለምን ገደልኩት?" እያለ ሁል ጊዜ ይፀፀትና ያዝን ነበር። ሁል ጊዜ ያለቅስና ያንጎራጉር ነበር። ከጊዜ ወደ ጊዜም ሃዘኑና ፀፀቱ እየበረታበት በመምጣቱ ግጥም እየደረደረ ያለቅስ ነበር። ሃዘኑ ግን ግጥም እየገጠመ በማንጎራጎርና በማልቀስ ብቻ ሊታገስለት አልቻለም። ስለዚህ ሃዘኔን የምገልፅበት የሙዚቃ መሳሪያ ያስፈልገኛል በማለት ያስብ ነበር። በመሆኑም ኦቴኖ በመጀመሪያ የሠራው "ቶም" የሚባል የሙዚቃ መሳሪያ ነበር። ቀጥሎ የሰራው ደግሞ ክራር ነበር። ኦቴኖ አንድ ጊዜ ቶም ሌላ ጊዜ ደግሞ ክራር እያቀያየረ የጊሎን ስም እየጠራ "ማረኝ . . . አጥፍቻለሁ ይቅር በለኝ . . . " እያለ ግጥም እየደረደረ ያለቅስና ያዝን ነበር። ስለዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ ሠርቶ ሌት ተቀን በግጥም ቶምና ክራር እየመታ፣ እያንጎራጎረ ያዝን በነበረበት ጊዜ ኦጌም አመጽ፣ አይሎ ተነሳበት። ቀጥሎም ውጊያ ተቀሰቀሰ። ውጊያው እንደተቀሰቀሰ አሁንም ኦቴኖ ብቻውን መዋጋት ጀመረ። ወዲያውም ከዚያ በፊት የማይታወቅ "ዴም" የሚባል ጦር ከብረት አፈር አቅልጦ ሠራ። ኦቴኖ የብረት ጦር ሠራ። እሱ የሰራው ጦር "ዴም" ይባላል። ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን ይህን ጦር የሠራው ኦቴኖ ነው። ይህን የሠራውን የብረት ጦር ይዞ ብዙ ሕዝብ ፈጀ። በመጨረሻም ድል አደረገ። ሕዝቡም እንደገና ተበታተነ። ኦቴኖ ብረት የሠራበት

ቦታ በኦፔኖ (በባሮ) አካባቢ ይገኛል። ዛሬ "የኦቴኖ የብረት መሥሪያ" እየተባለ ይጠራል።

ሕዝቡ ተበታትኖ ከሄደ በኋላ እንደ ገና ቶምና ክራሩን እየመታ ለጊሎ ማዘንና ማልቀሱን ቀጠለ። ሕዝቡ ደግሞ በሌላ በኩል "ምን ብናደርግ ኦቴኖን ልናሸንፈው እንችላለን?" በማለት በየዊማቹ፣ በተገናኙበት ቦታ ሁሉ መመካከር ያዘ። ኋላ ኦቴኖ የሠራውን ጦር "እኛስ ለመሥራት አንሞክርምን?" አለና ብረት ያለበትን አፈር በየቦታው እየፈለገ ለማግኘት ሞከረ። በመጨረሻም ብረት ያለበትን አፈር በማግኘቱ ኦቴኖ የፈለሰፈውን "ዴም" የተባለውን የብረት ጦር በብዛት ለመሥራት ቻለ። ከዚያ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ ጦርነት ተነሳ፣ ኦቴኖም ራሱ በሠራው ጦር ተወግቶ ሞተ። ያገሩ ሰውም አከላቱን በሙሉ ቆራርጦ በየቦታው ጣለው። እጁን፣ እግሩን፣ አንገቱን፣ የሠራ አካላቱን ቆራርጦ ጥሎት ሄደ። ግን ወዲያው ተቆራርጦ በየቦታው የተጣለው የኦቴኖ አካላት ተጠረቃቅሞ፥ እንደ ገና በአንዳች ተአምር ተገጣጥሞ ነፍስ ዘራ። ካንገቱ በላይ ያው ኦቴኖ ነው። ከአንገቱ በታች ግን ዘንዶ ሆነ። ካንገቱ በታች ዘንዶ የሆነው አካላቱ የእሳት ነበልባል ሆነ፣ የማይጠፋ እሳት። ከዚህ በኋላ በልቡ እየተሳበ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረ አኙዋን በእሳት አነዳደት። ዙሪያውን በተቀጣጠለው የእሳት ሰደድም የአገሩ ሰው ሁሉ በሽብር ተዋጠ። ብዙ ሰው አለቀ። ሰው መድረሺያ፣ መውጪያ፣ መግቢያ አጣ። ደኑ፣ ዱሩ፣ ሳር ቅጠሉ ሸለቆው፣ መንደሩ ሁሉ ጋዬ። በዚህ ጊዜ አካንጎ ወደ እሳት ዘንዶነት ተለውጦ አገሩን በማጥፋት ላይ የነበረውን ኦቴኖን ሂዳ ለመነችው። እያለቀሰች ተማፀነችው። ከፊቱ ወድቃ "ተው ኦቴኖ! ተው-ተው-ተው! ሕዝብ ፈጀህ፣ ጊሎን ገደልክ፣ አሁን አኙዋን በሙሉ ልታጠፋት ነውን? ተው አኙዋን አታጥፋት!" ብላ እያለቀሰች ለመነችው። በዚህ ጊዜ ኦቴኖ ከእሳት ዘንዶነት ሙሉ በሙሉ ወደ ድሮው አካላቱ ተለወጠ። አካንጎም በፍርሃት ተውጣ ስታየው ከቆየች በኋላ ኦቴኖ እንዲህ ብሎ ነገራት። "እሺ፣ አሁን በቅል ከትተሽ ወደ ውሃ ጣይኝ" አላት። አካንጎም ትልቅ ቅል አምጥታ ኦቴኖን ከትታ ኦፔኖ፣ ባሮ፣ ወንዝ ላይ ጣለችው። ከዚህ በኋላ አገሩ ሰላም ሆኖ ኖረ። ግን ብዙ ጊዜ ሰላም ሆኖ ከኖረ በኋላ "በሱዳን ጠረፍ ኦቴኖ ወደ ነጭነት ተቀይሯል" ተብሎ ወሬ ተወራ። "ወደ ነጭነት ተቀይሮ ተመልሶ መጣ" ተባለ። በዚህ ጊዜ እንደ ገና አኙዋ በሽብር ተዋጠች። የጭሮ፣ የኦዶንጎ፣ የአኮቦ፣ የጆር ሌላው ቀርቶ የፑኝዶ አኙዋ ሁሉ ወደ አቦቦና ወደ ዲጋው በሽብር ለቆ ተሰደደ። ኋላ ቆይቶ ሲረጋገጥ ግን በሱዳንና በእኛ ድንበር አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ የመጣው የእንግሊዝና የግብፅ ጦር መሆኑ ታወቀ። አገሩም እንደገና ሊረጋጋ ቻለ።